# የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ዘመን

… ያ ንጉስ። ወንድሜ ስለ መሃረቦቹ እየነገረኝ ነበረ፡ እና በካንሰር በሞት አፋፍ ላይ ለደረሰ ሰው ናቸው ብሎኛል። ስለዚህ ከአፍታ በኋላ እንጸልይላቸዋለን። [ወንድም ኔቪል “ከርቀት የተላኩ ሁለት ጥያቄዎች አሉ፡” ብሎኛል።—አርታዒ።] ሁለት ጥያቄዎች? እሺ፡ ይሁን… [አንደኛው። የጸሎት ጥያቄ ነው።”] እሺ፡ ጌታዬ። እነዚህም እንዲጸለይባቸው እዚህ አስቀምጣቸዋለሁ።

2 ሌላ ሰውም ማስታወሻ አስተላልፏል፡ መጥቶ ነገ እዚህ ስለሚኖራቸው ጉባኤ… ማስታወሻ አስተላልፏል። እንግዶቻችን የሆናችሁ፡ ነገ ከሰዓት ሁለት ሰዓት ላይ ቴፕ የሚያዳምጡበት ጉባኤ ስለሚያዘጋጁ፡ ከሰዓት እንድትገኙልን፡ በደስታ እንጋብዛችኋለን። ሌላ ሰራ ከሌላችሁ፡ ከዚህ በፊት ሰምታችሁት የማታውቁትን መልእክት—ያጫውታሉ የጸሎት ጉባኤም ይደረጋል፡ እና—እና ነገ ከሰአት በኋላ ሁለት ሰአት ላይ ጥሩ ጊዜ እንጠብቃለን። ለኔ ግን ነገ፡ እያችሁ፡ ለእሁድ ጠዋት እና ለእሁድ ማታ እንዲሁም ለነገ ማታ መዘጋጀት ስለሚኖርብኝ፡ በተጨማሪም፡ እንዲሁ፡ ስለ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ በሙሉ ማየት ስላለብኝ፡ የተጣበበ ጊዜ ይሆንብኛል።

3 እና አሁን፡ እሁድ ጥዋት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ታላቅ ጊዜ እንጠብቃለን፡ ምክንያቱ እሁድ ጥዋት የሰራ ቀን ስላልሆነ፡ ምናልባትም ከቅዳሜ ማታ ጀምሮ… የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን እንማራለን። እሁድ ጠዋት ግን **ስነፏ ድንግል፡** በሚል ርዕሰ እና፡ **የአንድ መቶ አርባ-አራት… አራቶቹ፡ ትንሳኤ** በተመለከተ፡ እና ለእሁድ ጥዋት የመልእክቱ ክፍተቶችን የሚሞሉ ትንንሽ ማስርያዎች በተመለከተ እንማራለን። ጉባኤው ከዘጠኝ ሰዓት ላይ ይጀምራል። ልክ ነው፡ ፓስተር? እሁድ ጥዋት፡ በዘጠኝ ሰዓት፡ እንደ እነዚያን ነገሮች ሁሉ ማንሳት እንፈልጋለን “ስነፏ ድንግል ምን ገጠማት፡ ልባሟ ድንግል ምን ገጠማት? መቼ ይመለሳሉ? ወይስ መቶ አርባ-አራት ሺዎቹ የት ይከሰታሉ?” ለእሁድ ጠዋትም ከዚህ መልእክት ጋር የሚሄዱትን፡ እንደዚያ ያሉ ብዙ ነገሮች፡ አንድ ላይ ለማያያዝ እንሞክራለን። ከዚያ በኋላ እሁድ ምሽት የመጨረሻውን ታላቅ መልእክ እና የሎዶቅያ መልእክት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ እሁድ ማታ እንማራለን።

4 ስለዚህም፡ አሁን፡ የነገ ከሰአት አገልግሎት፡ የቴፕ አገልግሎት ይሆናል። ወንድም ጂን… ነገ ከሰአት በኋላ ሁለት ሰዓት ላይ እንጀምራለን ብሎኛል። እና እናንተ መልእክቶቹን ለመሰማት በመሰውያው አጠገብ ለመጸለይ፡ መምጣት የምትፈልጉ ሰዎች፡ እናንተም መንፈሰ ቅዱሰን ወይም የሆነ ነገር የምትፈልጉ ሁላችሁ፡ ድንቅ ጊዜ ይሆናል። ቤተክርስቲያን በማንኛውም ጊዜ ገብቶ መጸለይ እና የጌታን ፊት ለሚፈልግ ለማንኛውም ሰው ክፍት፡ እና ሞቹ፡ ዝግጁም ነች። ቤተክርስቲያን በሯን ከፍታ ትጠብቃለች። እና እኛም… እንጠብቃችኋለን፡ በዚህ መልኩ ተረዱት፡ ነገ ከሰአት እንጠብቃቿለን።

5 በማንኛውም ጊዜ ለመጸለይ ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት በምትፈልጉበት ጊዜ ሁሉ፡ እንዲሁ፡ ሁሌ የተዘጋጀች ናት። ምናልባት በሮቹ ከተቆለፉ ወይም ሌላ ነገር ከሆነ፡ ከመንገድ ማዶ፡ እዚያ አካባቢ፡ የሚኖረው

ጥበቃው ወንድሜ አለ። 411 ይመስለኛል፡ እርግጠኛ ነኝ... ወይም 811 (እንደዚያ ነው... ? ) 811 ላይ፡ ከዚህ ቤተክርስቲያን በተቃራኒው በጎን በኩል ይገኛል፡ 811። ምናልባት እሱ፡ ከ... ከሚስቱ ጋር ከዘጉት እሷም ቁልፍ ሊኖራት ይችላል፡ ነገር ግን ከጠዋት ጀምሮ ክፍት ያደርጉታል፡ ይከፈታል። ያው፡ ልጆች እንዳይሯሯጡበት፡ ምናልባትም፡ መስኮቶችን እንዳይሰባብሩ፡ ታውቁታላችሁ፡ በተለይ ዛሬ ዛሬ፡ ህጻናት እንዴት እንደሆኑ ታውቃላችሁ፡ ስለዚህ ማታ ከፕሮግራም በኋላ ይዘጋል። የምንዘጋውም በዚህ ምክንያት ነው። ይሁን እንጂ የቤተክርስቲያን በር በማንኛውም ጊዜ መዘጋቱን አንወድም። ምናልባት ሌላኛው ሲስተካከል እንገባበታለን፡ ያኔ ሌላው ሁሉ ትክክል ይሆናል፡ እኛም... ሰዎች መጥተው እንዲጸልዩ፡ ፈውስም መንፈስ ቅዱስም እንዲፈልጉ፡ ሁሌም አንድ ሰው በቦታው እናስቀምጣለን።

6 እናንተም፡ በሕይወታችሁ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሌላችሁ ሰዎች፡ መጥታችሁ፡ መቆየት፡ ቢያስፈልጋችሁ አዳር ማደር፡ እስክትቀበሉት ድረስ መቆየት ትችላላችሁ።

7 ከትንሽ ጊዜ በፊት እዚህ፡ "ጋድ ኦል ኦቨር ሚ፡ ኤንድ ጋድ ኤቭሪ ዌር" እያለ ሲዘምር የነበረው ማን ነው? ንጥቀት የደረሰ መስሎ—ኝ፡ ሰዎች ሁሉ በዙርያዬ መኖራቸውን ለማየት፡ ዙርያውን፡ አየሁት። በእውነት ደስ ይላል፡ አመሰግኛለሁ። ቢያስፈልገን በየትኛውም ጊዜ ቆመን መዘመር እንችላለን። አዎን፡ ወዳጄ። ያ ነው... ያን ለመስማት፡ ወደ ውስጥ ገባሁ።

8 እና በጉባኤዎች የሚዘመሩ ጥሩ ዝማሬዎች ሁሉ ያመልጡኛል የዚህ ምክንያትም... ኦህ፡ እንዴት እንደሆነ ታውቁታላችሁ፡ ስራ ስለሚበዛብኝ ነው። ሰዎች—ብዙ ሰዎች እውሮፕላን፡ በባቡር፡ እንጂ... አያችሁ፡ መገመት—አትችሉም፡ ምክንያቱ በስልክም ይመጣልና፡ ወደ እነዚህም ሁሉ፡ መሄድ፡ መቀበል እና መጸለይ ይጠበቅባችኋል። ያለማቋረጥ ትሄዳላችሁ፡ በዚያ ላይ ማጥናት ይጠበቅባችኋል፡ እጅግ ከባድ ያደርገዋል። እንግዶች ማስተናገድ መቻላችን እና የቻልነውን ነገር ስናደርግላቸው ሁሌም ቢሆን ደስተኞች ነን... ምክንያቱ... በዚህ ዘመን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕዝቡ አገልጋዮች ነን። አሁንም ካደረግነው አብልጠን ማድረግ እንፈልጋለን፡ ይሁን እንጂ አንችልም።

9 ዛሬ ጠዋት፡ አንድ ጥሩ ወዳጅ፡ አገልጋይ ነው፡ በጭንቀት መንቀጥቀጥ የደቀቀ አቻኩለው አገቡት። የዚህ ሁሉ መንስኤው... ከመጠን በላይ በስራ መጠመድ ነው። እንደ... መነሣት ጀመረ፡ ትንሿ ልጁ ክፍሉ ውስጥ ቆማለች፡ እና መሽከርከር ጀመረችበት። ቀይ ፒጃማ ለብሳ ነበር፡ እንደተናገሩት መጨረሻ ላይ የሚያስታውሰው ነገር ትንሽ ቀይ ነጥብ፡ ዙርያውን እንዲህ ሲዞር፡ ሲዞር፡ ሲዞር፡ ሲዞርበት ነው። ከዛ ነቀለ፡ አያችሁ። ወድያውም አቻኮሉት። ስለዚህ መንስኤው—የስራ መደራረብ ነው፡ አያችሁ። እና አካላዊ ሰዎች መሆናችሁን—አትርሱ—አሁንም ፍላጎታችን... ሸክም ሁሉ በእኛ ላይ እንደተጫነ እናስባለን። ይሁን እንጂ፡ አያችሁ፡ እግዚብአብሔር አንዳንድ ሰራዎች የሚሰሩለት አገልጋዮች በየሰፍራው አሉት፡ ስለዚህ የቻልነውን ያህል ብቻ እናደርጋለን። ይህ በጎ አገልጋይ ግን በዚህ በመጨረሻ ዘመን ለጌታው የሚችለውን ሁሉ ለማድረግ ሞከረ። እርግጠኛ ነኝ... እግዚአብሔርም በዚያው አዳነው፡ ደህና ነው፡ እናም ወዲያውኑ መለሰው፡ እንደተለመደው፡ በደህና፡ ደስ ብሎት፡ መንገዱን ሄደ።

10 እና፡ አቤት፡ ዛሬም ታላቅ ነገር ሆነ። በርግጥ በእነዚያ ነገሮች ላይ መጀመር አልፈልግም፡ ነገር ግን... ታውቃላችሁ፡ ለባለቤቴ ነገርኳት፡ እንዲህ ብዬ፡ “አሁን፡ አንድ ሰው ይመጣል፡ እርሱም፡ አጭር፡ ወፍራም፡ ጠቆር ያለ ጸጉር እና ጥቁር አይኖች ያሉት ሰው ነው፡ እርሱ እነዚያን ምልክቶች ማንበብ ሲጀምር... አንቺ ጥሪው፡ አየሽ።” “ምክንያቱ ከጌታ ዘንድ መልዕክት አለው፡” አልኳት። እኔም መጽሐፍ ቅዱሰን ከፍቼ፡ እንዲህ አልኳት፡ “ጌታ እንዲያደርግ የሚፈልገው ያ እንደሆነ አንቺ እንድታይ እነዚህን ነገሮች እዚህ ላይ እንዲህ እዘረጋቸዋለሁ።”

11 ከሰምንት ዓመት በፊት፡ በፖላንድ ያደገ፡ ፖላንዳዊ የፖላንድ ሰው ነበር... በጉባኤው ላይ፡ ወደ መድረክ መጣና እንዲህ ተነገረው... ወይም መንፈስ ቅዱስ አይቶት፡ “አሁን አንተ ግራ ተጋብተሃል፡” በማለት፡ ተናገረው። ያኔ... እኔ የተናገርኩት መሰለው፡ ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ ነበር። በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ አብሮት ነበረ፡ በመጨረሻ ትናንት ማታ ከካንሳስ ከተማ ወደ ህንጻው አመጣው፡ ከዚያም ሰለ ውኃ ጥምቀት ሲሰማ ግራ ተጋባ። ወደ ሆቴሉ ሄደ፡ መንፈስ ቅዱሰም “አሁን ተነሰተህ ወደዚያ ውጣ፡” አለው። አንድ ሰው አብሬህ ልሂድ ብሎት ነበር፡ በራዕዩ ውስጥ ለብቻው ሰለነበረ ግን አይሆንም አለው። አያችሁ? እና... ይህ፡ ጨዋ-ሰው ምልክቶችን ማንበብ ሞከረ፡ እና ወደ ኋላ መመለስ፡ ጀመረ፡ ሚስቴም ጠራችው እና እኔም ወደ በሩ ወጣሁ፡ “እሱ—እሱ ራሱ ነው፡ አሰገቢው፡” አልኳት።

12 ነገሩን ከተረዳ በኋላ፡ “አሁን አይቼዋለሁ፡” አለኝ፡ “ምን ላድርግ? ” አለ።

“አየህ፡ አሁን ታውቅ ዘንድ ይህን ላሳይህ እፈልጋለሁ፡” አልኩት። “አንተ እንደምትመጣ ጌታ አሰቀድሞ ነግሮኛል፡” አልኩት። እሱን መጠየቅ ትችላላችሁ። “አሁንም፡ ቃሉ በፊትህ ነው። ከመሄድህ በፊት ይኸው አሁን አንብበው፡” አልኩት።

13 እና፡ አሁንም በኢየሱስ ክርሰቶሰ ሰም ሊጠመቅ እዚህ ተገኝቷል። ሰለዚህ... ?... እንደሚመሰለኝ፡ አሁንም ውሰጥ ቁጭ ብሏል። እዚህ ነህ፡ ወንድሜ? ወንድማችን፡ ፖላንዳዊው ወንድም። ኧረ? አዎን፡ ከኋላ ጥግ ላይ አለ፡ አዎን። ቁምና... እንዲያዩህ እጅህን ወደ ላይ አንሳ። መልካም። መንፈስ ቅዱስ ሲሰራ ማየት... ይህ በተደጋጋሚ የሚከሰት ነገር ነው። ብዙ ሰዎች ራእዮች የሚመጡት መድረክ ላይ ብቻ ነው ብለው ያሰባሉ። ኦህ፡ ከዚያ አይጀምርም። ታዲያ፡ እነ ወንድም ሊዮስ? በሁሉም ቦታ አለ፡ አያችሁ። እንደውም፡ ትንሹ ቦታው፡ ይህ ነው። እዚህ ላይ የሚታየው አነሰተኛ ነው። ቀን እና ሌሊት የሚመላለሰው በውጭ ነው፡ አያችሁ። አዎን፡ ባለቤቴን ጠይቁ፡ እሷ... ወይም ሌሎች፡ ጎረቤቶቼ፡ እነ ወንድም ዉድ፡ እና በዙሪያዬ ያሉትን ሁሉ ጠይቁ። ኦህ፡ ማይ! እዚህ የሚመጡት—ትንንሽ ነገሮች ብቻ ናቸው፡ በውጭ የሚከሰቱ ግን ታላላቅ ነገሮች ናቸው። እንደውም፡ ግማሹን ያህል እንኳ አልተነገረም። ኦህ! ጌታችን በቅርቡ እንደሚመጣ እና ከእርሱ ጋር ዘወትር እንደምንሆን ሰለ አወቅን፡ በዚህ እጅግ ደስ ይለኛል፡ **ዘላለም** ነው እንጂ፡ **ዘወትር** አይደለም፡ ለዘላለም።

14 አሁን፡ እንደ ጌታ ፈቃድ፡ የዛሬ ሳምንት እሁድ፡ አሰራ ሰምንት፡ እንደሆነ አምናለሁ። የዛሬ ሳምንት፡ እሁድ፡ አሰራ ሰምንት ነው። ሰይጣን ይህ የሚዘዋወር ጉንፋን ሊያቀብለኝ ፈልጎ፡ ከባድ ውግያ አሳልፌአለሁ፡ ደጋግሜ

አቀብለዋለሁ፡ ይመልሰልኛል፡ እንደገና አቀብለዋለሁ። ስለዚህ... ረዘም ያለ ውግያ አጋጥሞኛል። ስለዚህ በሚቀጥለው ሳምንት ጨርሰን እንዋጋዋለን። ጌታ ቢፈቅድ፡ ቀጣይ እሁድ፡ በአሥራ ሰምንት፡ ይሆናል። ለታመሙ ሰዎች ለመጸለይ ጉባኤዎችን ለማመቻቸት እንሞክራለን ምክንያቱ... ነገሮች እየተከማቹ እየተከማችሁብን ስለሆነ ፈጣን እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች በቻልነው ፍጥነት ለማስተናገድ እንሞክራለን፡ የሚመጡልን ሰዓታት፡ እና የሚሄዱትን የማታ ሰዓትታ እና ሌሎች ሁሉ እንጠቀማለን። ስለዚህ በአሰራ ሰምንት መደበኛ የፈውሰ አገልግሎት ይኖረናል። ስለዚህ እንዲጸለይላቸው የምትፈልጓቸው ወዳጆች ካሉ፡ ያን ጊዜ፡ አምጧቸው፡ ወይም ይዛችኋቸው ኑ።

15 ዛሬ፡ ብዙ የጀፈርሰንቪል ወዳጆቼ እንደነገሩኝ፡ አምሰት (ወይም ሰድሰት) ሰዓት አካባቢ ተነሰተው፡ እዚህ ለመድረሰ በጊዜ መጥተው፡ ለመኪኖቻቸው ማቆሚያ እንዳላገኙ ነግረውኛል። እነርሱንም... "መቼም... እነዚህ ሁሉ፡ ከተለያየ ቦታ ሊጎበኙን የመጡ ወንድሞች፡ ሰዎች፡ እና አገልጋዮች ናቸው፡" አልኳቸው። "በእነዚህ አሰተምህሮቶች ላይ—እየተመረኮዙ የሚገኙ ናቸው፡" ብዬ ነገርኳቸው።

16 አሁንም ዋና ዋና ነጥቦችን ለመዳሰሰ እየሞከርን ነው። ምናልባት ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ለምን፡ እናንተም እንድታነቡት—በመጽሐፍ መልክ ማሳተማችን አይቀርም—የሚጨመርበት ጥቂት ነገር ይኖራል፡ ምክንያቱ በየምሽቱ... ካስተዋላችሁ፡ ባለፉት ትቂት ምሽቶች፡ እንዳያችሁት፡ ድምጹን ለማሰቀመጥ፡ እየተጋሁ፡ ነበር፡ ምክንያቱ እንድታዩት የምፈልገው፡ ዋናው ነገር፡ በዚህ ዘመን የተሰጠ፡ እርሱ ማን እንደሆነ፡ የሚያሳይ የክርሰቶሰ መገለጥ አለ።

17 አሁንም፡ ቅዱሳት መጸሕፍትን ማንበብ ከመጀመራችን በፊት... ነገ ለቅዳሜ ማታ ሁላችንም አሰቤዛዎቻችን የምንገዛበት ታላቅ የገበያ ቀን እንደሆነ አውቃለሁ። ስለዚህ ቅዳሜ ምሽት በነጻነት ወደ ቤተ ክርሰቲያን ለመምጣት፡ እንዴ፡ ቅዳሜ ከሰአት በኋላ ወይም ቅዳሜ ጠዋት ልንገበይ ይገባናል። ነገ ሳትደክሙ መግዛት እንድትችሉ ዛሬ በጊዜ እንለቃችኋለን፡ ሰለዚህ ቴፑን ከያዙት ከእነዚህ ወንድሞች ጋር ለከሰዓት—እና ለነገ ምሽት ፕሮግራም እዚህ ለመገኘት ትመለሳላችሁ።

እሰኪ፡ ፈቃዳችሁ ከሆነ፡ ለጸሎት ሁላችንም በእግሮቻችን እንቁም።

18 ከመጸለያችን በፊት፡ ልዩ የጸሎት ልመና ያለው ሰው እዚህ ካለ፡ ምናልባት፡ እንዲታወቅላችሁ የምትፈልጉ ካላችሁ እጃችሁ ከፍ እንድታደርጉ አሳሰባለሁ። እግዚአብሔር ያያል። አሁን በችግረኛ ዓለም ውሰጥ መሆናችንን ወይም አለመሆናችንን ተመልከቱ፡ ወንድሞች። ዘጠና-አምሰት ወይም ዘጠና-ሰምንት በመቶው ታዳሚ እጆቻቸውን ያነሱ ይመሰለኛል... አሁን፡ አሰታውሱ፡ እግዚአብሔር ሳያውቀው መንቀሳቀሰ እንኳን አትችሉም። አያችሁ? ሃሳባችሁን ያውቀዋል፡ የምትለምኑትን ለምን እንደሆነ ያውቃል።

ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ፡

19 ቸር የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ እሰማችኋለሁ ብለህ በገባህልን ቃል መሰረት፡ ወደ ቅድሰናህ፡ ወደ ዙፋንህ በፊትህ ቀርበናል። ብናምን ደግሞ፡ የጠየቅነውን ትሰጠናለህ። ሰህተቶቻችንን ሁሉ አሁን እንናዘዛለን። ጌታ ሆይ፡ ለየትኛውም አይነት በረከትህ—የተገባቸው አለመሆናችንን፡ ተገንዝበናል።

የተገባን—አይደለንም። ሁላችንም በአንድነት የተገባ አይደለንም፡ አንዳች ጥሩ ነገር እንደሰሩ—የተገባቸው መስለን—አልመጣንም። አባት ሆይ፡ ታላቅነትን ሁሉ ከእኛ የሚያስወግድ፡ ቀራንዮን ስንመለከት፡ ከክርስቶስ እርሱም ከመሰቀሉ በቀር ሌላ ነገር እንደማናውቅ—እንገነዘባለን። ከዚያ በኋላም እንደ ቅዱስ ቃል መሰረት፡ ስለ ጽድቃችን በሶስተኛው ቀን መነሳቱን፡ በመጨረሻው ዘመን በሰማይ እስኪገለጥ ድረስ በውስታችን እንዲያድር፡ ከአርባ ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ መልክ ተመልሶ መጣ። አሁንም የመጨረሻ ጊዜ አሁን በፍጥነት ሲቃረብ እናያለን። ጌታ ሆይ፡ ይህን የመሰለ ታላቅ ዕድል ስለሰጠኸን፡ እጅግ ሲበዛ—ደስተኞች ሰዎች ነን።

20 አባት ሆይ፡ ይህ አድማጭ ታዳሚ ሁሉ፡ ልቡን ዝቅ አርጎ ለማዳመጥ ስለተቀመጠ፡ እጅግ አመሰግንሃለሁ... ? ... በተጨማሪም፡ ጌታ ሆይ፡ ዘወትር ከህዝብህ ጋር ለመነጋገር ወደዚህ ፑልፒት ስመጣ፡ ዘወትር ማታ እና አሁንም ቢሆን አፌን እንድትቀድስልኝ እጸልያለሁ፡ ምክንያቱም፡ ጌታ ሆይ፡ ክፋ እንድናገር ፈጽመህ አትተወኝ። በዳንኤል ዘንድ በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ እንዳደረግከው አሁንም አፍን የመዝጋት ኃይል አለህ። እንደ ፈቃድህ ያልሆነውን ነገር መናገር ቢዳዳኝ፡ ጌታ ሆይ፡ እንዳልናገር፡ አፌን ዝጋ። ጌታ ሆይ፡ የእኔ አሳቦች ከልክለህ፡ ከእውነት በቀር ሌላ ነገር በማልናገርበት፡ ትክክለኛ መስመር ውስጥ አስገባኝ። በዚያ በታላቋ ቀን እነዚህ ሰዎች ሁሉ በዚያ እንደሚጠብቁኝ ተረድቻለሁና... እኔ እንደሰበኳቸው አገልግሎት መጠን ይጠባበቁኛልና። ከከዋክብትህ፡ እና መላእክቶችህ፡ አገልጋዮችህን ከባሪያዎችህ፡ አንዱንም ለመውሰድ—ስትመጣ፡ እዚህ በሰበክናቸው ስብከቶች መሰረት በማድረግ ሁሉንም የሚመዘኑ ይሆናሉና። ባርያዎችህ፡ ተጠያቂነትን እንዲሸከሙ ታደርጋቸዋለህ።

21 አሁንም፡ አባት ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስ እንጂ ሰው እንዳይናገር እጸልያለሁ። እንድንሰማው ልባችንን ግረዝ። አባት ሆይ፡ እኔም እሰማለሁ። የታመሙትን እና የተጎዱትን እንድትፈውስ እጸልያለሁ። በሁሉም ቦታ የሚገኙትን፡ የተቸገሩትን ሰዎች ሁሉ፡ ጸጋህና ምሕረትህ ከእነሱ ጋር ይሁን። ዛሬ ማታ በተነሡ እጆች የቀረቡትን ልመናዎች በሙሉ መልስ ያግኙ። እንዲሁም እነዚህ መሃረቦች የሚወክሏቸው፡ በመላ ሀገሪቱ እየተሰቃዩ ያሉ ግለሰቦች፡ እና እነዚህ በእጄ የተቀመጡ የጸሎት ጥያቄዎች፡ አባት ሆይ፡ ህመምተኞችን ፈውሳቸው፡ መንፈስ ቅዱስም ልመናቸውን ይመልስ። አሁንም በተጻፈው ቃልህ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተናገረን፡ በኢየሱስ ስም ጸለይን። አሜን። አረፍ አረፍ በሉ።

22 አሁን፡ ዛሬ ማታ ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ትንሽ ይሞቃል። ወደ ታላቁ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን እየተቃረብን ነው። ዛሬ ማታም ሌላኛው ታላቅ የቤተክርስቲያን ዘመን—አምስተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን እንመለከታለን። የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ዘመን አይተናል፡ እርሱም ኤፌሶን ነው። መጀመሪያው ላይ እነዚህን እንደገና አነባቸዋለሁ፡ ሁሉንም ተጽፈዋል ስለዚህ ማስታወሻዎቻችሁ ላይ መፈተሽ እንድትችሉ ላነብላችሁ እወዳለሁ።

23 የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ዘመን የኤፌሶን ቤተክርስቲያን ዘመን ነበር፡ ከ55 እስከ 170 **ዓ.ም**. ነበር። ጳውሎስ ኮከብ ሲሆን፡ የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ዘመን ይህ ነበር። እግዚአብሔርም "ያለፍቅር ስለነበረው ስራቸው" ነቀፋቸው። ሽልማታቸውም "የሕይወት ዛፍ" ነበረ።

24 ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ከ 170 እስከ 312 ሲሆን፡ የዘመኑ መልእክተኛ ኢራኔዎስ ነበር። ነቀፌታቸውም ሰደት-... መከራ፡ እና የምትሰደድ ቤተክርስቲያን ነበረች። ሽልማታቸውም፡ “የሕይወትን አክሊል” ነበረ።

25 ሦስተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ጴርጋሞስ ነበር፡ ቅዱስ ማርቲንም የቤተ ክርስቲያኒቱ መልእክተኛ ነበር። የቤተ ክርስቲያኒቱ ዘመን ከ 312 እስከ 606 ነበር። ነቀፌታው “የኃሰት ትምህርት፡ የሰይጣን ውሸት፡ የጵጵስና አገዛዝ አመሰራረት፡ የቤተ ክርስቲያን እና የመንግስት ጋብቻ ነበር።” ሽልማታቸውም “የተሰወረ መና፡ እና ነጭ ድንጋይ” ነበረ።

26 አራተኛውም የቤተ ክርስቲያን ዘመን ትያጥሮን ናት፡ ኮሉምባ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዘመን መልአክ፡ መልእክተኛው ሲሆን፡ ከ 606 እስከ 1520 ነበር። ይህ የቤተ ክርስቲያንም ዘመን የጵጵሰና ማታለያዎች፡ የጨለማ ዘመን ነበር። (ትናንትና ማታ የነበረው፡ ታስታውሱታላችሁ፡ የጨለማው ዘመን።) እና የ—ሽልማቱ ነገርም፡ ለኮከቡ “አሕዛብን የሚገዛበት ኃይል፡ እና የንጋት ኮከብ፡” ነበር።

27 አሁንም፡ ዛሬ ማታ፡ አምስተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን እንጀምራለን፡ ሰርዴስ የቤተክርስቲያን ዘመን ነው፡ ሰ-ር-ዴ-ስ፡ ሰርዴስ። የዚህ ዘመን የቤተ ክርስቲያን መልእክተኛም ማርቲን ሉተር ነው፡ ዛሬ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ወይም በአስተማሪ፡ ወይም በምእመናን ዘንድ፡ ይበልጥ የሚታወቅ ሰው ነው። እናም ያ የቤተ ክርስቲያን ዘመን በ1520 ተጀምሮ በ1750 ያበቃል፡ ከ 1520 እስከ 1750፡ እናም ያን ዘመን “የተሃድሶ ዘመን” ብለን እንጠራዋለን። የዘመኑ ነቀፌታም “የገዛ ሰማቸው መጠቀማቸው ነው።” ለተረፉት ለጥቂቶቹ ቅሪቶች የሚሰጣቸው ሽልማትም፡ ይህ ነበር “ነጭ ልብሰ ለብሰው በፊቱ ለመመላለስ፡ እና ሰማቸውም በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ መሆን ነበር።” አሁንም ይህን በምናደርግበት ጊዜ ጌታ ይባርከን።

28 እንግዲህ በዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን በ3ኛው ምዕራፍ፡ 1ኛ ቁጥር እንጀምራለን። ለተሐድሶው ዘመን፡ ለሰርዴስ የተላከው መልዕክት። ሁሉ ለመጥፋት ተቃርቦ፡ ጥቂት የሚያምኑ ቅሪቶች ብቻ የነበሩበት።

29 አሁን እዚህ የተነገረው ነገር፡ ምናልባት አዳዲስ ለመጣችሁ ሰዎች ነው፡ ይህም... ከኋላ እንዳትቀሩ ነው። በርግጥ ተዘበራርቋል፡ እና ምናልባት አንድ ቀን መጥተን መልዕክታችንን ሰፍራውን እናስይዘዋለን... በደንብ ስለን፡ ከከሰዓት መጥተን እናስተካክለዋለን፡ ምናልባትም እሁድ እናስተካክላለን። አሁን፡ እነዚህ እያንዳንዳቸው-... የቤተ ክርስቲያንን ዘመን የሚወክሉ ናቸው፡ አንድ፡ ሁለት፡ ሦስት፡ አራት፡ አምስት፡ ሰድሰት፡ ሰባት። **ይህ** የሚጀምረው የፊላደልፊያ ነው...

30 እና **ይህ** ደግሞ—የጴንጤቆስጤ ኃይል፡ ወይም በጴንጤቆስጤ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን የሚወክል ነው። መጀመሪያ ላይ በጣም ትልቅ ቤተክርስቲያን ነበር፡ ነገር ግን በ—በ... መካከላቸው የኃይማኖት ተቋም መንፈስ አስጀመሩ፡ ይህም ቤተ ክርስቲያኒቱን ተቋም ለማድረግ ነው፡ መጠሪያውም “የኒቆላውያን ስራ” ይባላል። ከኋላ ያላችሁ እየሰማችሁኝ ነው? አዎን? እሰይ። “የኒቆላውያን ሰራ።” እንግዲህ፡ ገና **አስተምህሮ** አልሆነም ነበር። ከዚያም ቃሉን ወሰደን፡ “ስራ” ምን እንደነበረ፡ “ኒቆላውያን” ምን

እንደነበረ መርምረነዋል። እንግዲህ ይህ ኒቆላውያን፡ ለኛ እንግዳ ሰም ነው፡ ስለዚህ ግሪክኛን አመጣሁና መረመርኩት። እና **ኒቃኦ** ማለት “መውረር፡ ወይም ማሸነፍ፡ መጣል ማለት ነው።” ኒቆላውያን፡ **ላኦስ** ማለትም “ቤተ ክርስቲያን፡ ምእመናን” ማለት ነው። ኒቆላውያን፡ ምእመናንን ለመጣል፡ እና በረከቶችን በሙሉ ለመያዝ የሚሞከር ሰ—ሰራ፡ ከዚያም መጽሐፍ ቅዱሰን ለማንበብ፡ እና በውስጡ የተጻፈውን ለመተርጎም፡ ከቤተ ክርስቲያን ኃላፊ ወይም ከቢሾፑ ብቻ በቀር፡ ሌላ አይችልም የሚል ተግባር ነው።

31 በሁለተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን፡ አንቆ የሚይዝበት መንገዱን፡ እንደከፈተ እንገነዘባለን። **ይህ** አሁንም ጴንጤቆስጤ ሲሆን፡ **ይህ** ደግሞ የኃይማኖት ተቋም ነው (መ)።

32 አሁን፡ በሦስተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን፡ ማለት በጴርጋሞን፡ ጴንጤቆስጤ ታንቆ እስከ መሞት ደረሰ። የኃይማኖት ተቋም አስተምህሮ ግን፡ **እዚህ** ‘ከሰራ” ተነሰቶ፡ “አስተምህሮ” እከመሆን **እዚህ** ድረሰ ተጓዘ። ከዚያ በኋላ በትክክል፡ እዚህ ጋር በግልጽ ተጋቡ። ተጋቡ! ይ... ይህ ቡድን በጴንጤቆስጤ ወገኖችን ላይ የበላይነቱን ያዘ።

33 አሁንም ወንድሞች ሆይ፡ ይህ አባባሌ፡ ትክክለኛ እውነት ነው። የታሪክ ቅዱሳን ጽሑፎች መሠረት ያደረገ ነው። የኒቂያ ጉባኤ መጻሕፍት፡ **የፎክስ ቡክ ኦፍ ዘ ማርቲርስ፡** እና ሌሎች ታላላቅ ጥንታዊ ጽሑፎች ጭምር። በጣም ጥንታዊ የሆኑ የእጅ ጽሑፎች አግኝቻለሁ። እና ለሁላችሁ... እናገራለሁ... ጴንጤቆስጤ ነኝ እያልኳችሁ አይደለም። “ጴንጤቆስጤ” ብዬ ሰናገራችሁ፡ ይህ እኛ በምንኖርበት ዘመን ያለው ድርጅት ማለቴ አይደለም... እንደዚያ ማለቴ አይደለም። ያ’ማ እንደሌሎቹ ሁሉ ጥፋተኛ ነው። ከእውነተኛው የእግዚአብሔር መንፈስ ከዋናው ትምህርት ጋር፡ ከዋናው በረከቶች ጋር፡ ከዋናው ሰዎች ጋር፡ ልክ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው በመጀመሪያ ሲጀምር እንደነበረ ነገሮች ሁሉ ያለው፡ እውነተኛውን ጴንጤቆስጤ ማለቴ ነው።

34 እንግዲህ፡ **ወደዚህ** ዘመን ሰንመጣ፡ ጴንጤቆስጤ ምን ያህል እንደተጓዘ ታያላችሁ። ከኋላ ያላችሁ በትክክል ይታያችኋል? ማዶ ላይ ያላችሁሰ በደንብ ይታያችኋል? በጣም ጥሩ። አሁን፡ እዚህ ጋር፡ የትናንትና ማታው፡ **እዚህ** ከባዱ ዘመን ይመጣል፡ **ቆ-ሰ-ጠ-ን**፡ ቆሰጠንጢኖስ፡ ቆሰጠንጢኖስ፡ አመጣዋለሁ። ጣዖት አምላኪ፡ ሆኖ... **እነዚህን** (የኒቆላውያን አስተምህሮ የነበራቸውን) ክርስቲያኖችን እንዲት ጥያቄ አቀረበላቸው ጦርነቱ እንዳሸንፍ ከጸለያችሁልኝ እና አሸንፌ ከተመለሰኩኝ፡ በቃ፡ ክርስትያን እሆናለሁ አላቸው። ያን ጊዜ በጦርነት ውስጥ ሆኖ፡ ሕልም አይቶ ነበርና ይህም... ነጭ መሰቀል በፊቱ አየ፡ እነሆም፡ “በዚህ ታሸንፋለህ” የሚለውን ድምጽ ሰማ። ያም እውነት ነበረ። ከዚያም ሠራዊቱን ሁሉ ቀሰቅሶ በጋሻቸው ላይ ነጭ መሰቀልን ቀባ፡ እና ዛሬ፡ የኮሎምበስ ናይትስ በመባል የሚታወቀው፡ የካቶሊክ ሰርዓት የተወለደው ያን ጊዜ ነበር።

35 እ—አሁን፡ ሰለ ቆሰጠንጢኖስ፡ እርሱም... ሰለመለወጡ፡ ከታሪክ አንጻር አንዲት ነገር ማቅረብ አትችሉም። ጠማማ ፖለቲከኛ እንጂ ሌላ አልነበረም። መንግሥቱን አንድ ለማድረግ እና ጠንካራ ለማድረግ—ያለመ አሳብ በአእምሮው የያዘ ሰው ነበር። እሱ ራሱ፡ ጣዖታትን የሚያመልክ፡ አረማዊ ሆኖ፡

የኒቆላውያን አስተምህሮ ተረግጦ ወደ ጎን ሲጣል ተመለከተና፡ ትናንት ማታ ያየነውን ተመሳሳይ ስልት ተጠቀመ።

36 ኢየሱስም ይህ ከመሆኑ በፊት ከሦስት መቶ አራት ዓመት አስቀድሞ፡ የበለዓምን ትምህርት እንደሚያስተምር ተናግሯል። በለዓም የእስራኤልን ልጆች እንዲታለላቸው፡ እንዲያመነዝሩም እንዲደረጋቸው—እና ለጣኦታት... የሚያቀርቡትን ነገሮች፡ እና የሚበሏቸውን አቀረበላቸው። እንግዲህ፡ "ለጣኦት የተሰዋን መብላት፡" ምን እንደሆነ በደንብ እናውቃለን፡ አምልኮ ነው። ሄደውም፡ እስራኤል እንዲሴስኑ፡ ወደ ታላቅ የጣዖት በዓል እንዲሄዱ በማድረግ፡ ቀድሞ በልዓም እንደፈጸመው ስራ ሁሉ፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ጣኦታትን አስገቡ፡ በጣዖታት ፊትም ሰገዱ።

37 እንግዲህ፡ ቆስጠንጢኖስም በስልቱ ተመሳሳይ ነገር አደረገ፡ ቤተ ክርስቲያንም ሠራ። በኒቂያ ጉባኤ ብዙ ሰጠ፡ ከዚያም እነርሱ... የነበሩትን—ብዙ ታላላቅ ሕንጻዎች፡ እነዚህን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለወጣቸው። ከዚያም በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች ያጌጠ፡ ትልቅ የእብነበረድ መሠዊያ ሠራ። ወደ ላይም ከፍ በማድረግ በላዩ እንደ ዙፋን አኖረበት፡ እንዱንም ሰው ራስ አድርጎ አስቀመጠ... ሰውዬውም "ቢሾፕ" ተባለ። እናም በዚህ ዙፋን ላይ አኖሩት፡ ቦኒፌስ ሳልሳዊ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ። ተራ የገበሬ ልብሰ ለብሶ—እንዲሁ እንዲመላለስ አልተውትም፡ ታላቅ እና አማልክት የሚያስመስለውን ልብስ ደርበውለት—በዚያም እንዲቀመጥ አደረጉት፡ "ምትክ" ብለው ሰየሙት። ምትክ፡ ወይም **ቪካሪየስ ፊሊ ዴይ፡** "በእግዚአብሔር ልጅ ምትክ" ማለት ነው።

38 እንግዲህ፡ ጥበብ ያላችሁ ሰዎች፡ ይህን ሰዕል ስላችሁ፡ ጻፋት፡ **ቪካሪየስ ፊሊ ዴይ**። እና እዚህ ስር መሰመር ስላችሁ ቁጥሮቹን ስትደምሯቸው፡ እግዚአብሔር ስለ አውሬው ምልክት የተናገረው በትክክል ይህ ሆኖ ታገኙታላችሁ፡ ስድስት መቶ ስድሳ-ስድስት። አያችሁ፡ ቪካሪየስ ፊሊ... እንግዲህ፡ ሮም ሄጄ ቫቲካንን ጎብኝቻለሁ። እና በገሃነም፡ በገነት፡ እና በመንጽሄ ነፍሳት ስልጣን ያለው፡ ባለ ሶስት ደረጃ አክሊል አየሁ። አያችሁ? አክሊሉን፡ ልብሱን፡ ሌላውን በሙሉ፡ በዚያ አየሁት።

39 በርግጥ፡ ሐሙስ ከሰአት በኋላ በሦስት ሰዓት ላይ **የበቀደሙ** ጳጳስ ለማግኘት ቀጠሮ ነበረብኝ። ነገሩ የያዘው ባሮን ቮን ብሎምበርግ ነበር... እና እንዲህ አለኝ፡ "አሁን፡ ስትሄድ፡ ወንድም ብራንሃም፡ ማድረግ ያለብህ የመጀመሪያው ነገር በቀኝህ ጉልበት ላይ ተንበርክከህ ያንን ቀለበት መሳም ነው።"

40 "አይሆንም። አይሆንም። ተወው፡" አልኩት። እንዲህ አልኩት፡ "እኔ... በሰውዬው ላይ ምንም ችግር የለብኝም፡ በሱ... ?... " እኔ ግን አልኩት፡ "አንድ ነገር አለ፡ ለአንድ ሰው ማዕረጉን እሰጣለሁ፡ ለምሳሌ 'ሬቨረንድ' ቢሆንም፡ ችግር የለብኝም፡ 'ሽማግሌ፡ ዶክተር፡ ቢሾፕ፡' ምንም ቢሆን፡ ሰውዬውን በደስታ እቀበላለሁ። ለግሰብን መሰገድ ግን? ሰግደቴን፡ ለአንድ ሰው ለኢየሱስ ክርስቶስ አቀርባለሁ። በፊቱ የምሰግድለት ሰው እሱ ብቻ ነው።" "ብቻ ተወው። ስርዘው።" ይህን አላደርግም፡ አልኩት። ስለዚህ እኔ...

41 ወደ ቤት ከመጣሁ በኋላም ታላቁ አሜሪካዊ ቴዲ ሩዝቬልትም፡ እንዲሁ፡ አድርጎ እንደሚያውቅ ተረዳሁ። በምክንያት ፈቃደኛ አልሆነም… ይህን በታሪክ ታስታውሳላችሁ? ቀለበቱን መሳም ስላለበት ጳጳሱን ለማየት ፈቃደኛ አልሆነም… እንዲሁም፡ እያችሁ፡ በትልቁ ጣት ጭምር ነበራቸው። ስለዚህ… ኦህ፡ አይሆንም። አይሆንም፡ ተወው። ሆኖም…

42 እንግዲህ፡ እ… አሁን፡ ትናንት ማታ እንዳየነው… እንደ በልዓም፡ በ… እንግዲህ፡ መጀመሪያ፡ ከዚህ ከመነሳታችን በፊት፡ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ውህደት በመፍጠር ጋብቻ ፈጸሙ፡ ቤተክርስትያናቸው ውስጥ የነበሩትን ጣዖታት፡ አንዳንድ ጣዖታዊ እሳቤዎችን ተቀበለ። የጁፒተር አምላክ፡ የፀሐይ አምላክ፡ የማርስ አምላክ፡ የቬኑስ አምላክ፡ እነዚያንም የአማልክት ጣዖታት ሁሉ ከአረማውያን አብያተ ክርስቲያናት አመጣቸው፡ እና ጳውሎስ፡ ጴጥሮስ፡ ድንግል ማርያም፡ እና ሌሎች ሁሉ ተክቶ፡ እንዲህ አለ፡ “ኢየሱስ ጴጥሮስን ‘መክፈቻዎቹን እሰጥሃለሁ፡’ ብሎታልና፡ ይህም ሐዋርያዊ መተካካት ነው።” ይህ እስከ ዛሬ ድረስ የካቶሊክ ትምህርት ነው። ጣዖታትንም አቆሙ። እና ምን አደረጉ? የጣዖት አምልኮን ወደ ክርስትና አመጡ፡ እውነተኛ ክርስትና አይደለም፡ ክርስትና-ተብዬው ነው እንጂ፡ ምክንያቱም ትንንሽ ጴንጤቆስጤዎች…

43 አሁንም አስታውሱ፡ “ባፕቲስት፡ ሜቶዲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡” ማለቴ… አይደለሁም፡ እነዚህ በሁሉም ውስጥ ናቸውና። እውነተኛው፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር አዋጅ ግን ጴንጤቆስጤ ነው፡ ድሮም፡ ዛሬም፡ ወደፊትም ያው ነው! የቤተ ክርስቲያን ጅማሬ መነሻው፡ እዚሁ በጴንጤቆስጤ ኃይል ውስጥ ነው።

44 እንግዲህ፡ እናንተም “ትክክል ነው፡ ወንድም ብራንሃም፡” ትላላችሁ አይደል? ታሪክን ገልጣችሁ እስከ አሁን ድረስ ያለውን፡ ከጊዜ ፍሰት ውስጥ እንድትመረምሩት፡ እና እውነተኞች የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ፡ የጴንጤቆስጤ በረከትን ተካፋዮች ካልሆኑ መርምራችሁ ተረዱ፡ በልሳኖች ተናገሩ፡ ልሳኖችንም ተረጎሙ፡ ምልክትና ድንቅ ነበራቸው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። ሐዋርያቱ ያደረጉትን ነገር ሁሉ፡ አንዳች ሳያዛንፉ፡ እነርሱም አደረጉ። ታሪኩን ሳነብ፡ ጳውሎስን እና ኢራኔዎስን እና—እና—እና—እስከነ ቅዱስ ማርቲን ድረስ፡ ሌሎች ሰዎችም ሁሉ፡ ኮሉምባ፡ (እስከዚህ ዘመን ድረስ ያሉትን) የወሰድኩበት ምክንያት፡ ድንቅ እና ምልክቶች ስለነበራቸው ነው።

45 እሺ። ስለ እነሱ ተናግሯል… ማይኩ ትንሽ እያስቸገረ ነው… ይሄኛው ይሻላል? እሺ። አይ፡ ቢሊ፡ ራሳቸውን እየነቀነቁ ነው፡ በጭራሽ እየተሰማቸው አይደለም። በጣም ጥሩ። እስኪ ከቻልክ… ? ይሄኛው… ? አሁንስ፡ ይሰማችኋል? አሁንስ፡ ይሄኛው እንዴት ነው? የተሻለ ነው? አዎን? ሁሉም ሰው፡ “ደህና ነው” ይበል። ጳውሎስ፡ በእናንተ ላይ አንደኛው ምልክት ነው። በጣም ጥሩ። እሺ።

46 አሁን፡ በዚያ ዘመን ያኔ ይህን ታላቅ ነገር ባደረገ ጊዜ፡ ይህን ሰው በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ላይ ዓለም አቀፋዊ ጳጳስ አድርጎ ሾመ፡ ብዙ ገንዘብ እና ልዩ ልዩ ነገር ሰጣቸው፡ ቤተ ክርስቲያንን እና መንግሥትን አንድ አደርጋለሁ በማለት፡ ቃል ገባላቸው፡ ቤተ ክርስቲያን መንግሥትን እንድትቆጣጠር አደረገ።

እርሱን ታላቅ ሰው አደረገው። ይህ ማለት... በጨለማው ዘመን የተፈጸመ ነገር፡ ማለት፡ ቆስጠንጢኖስ ያደረገው ነገር በሌላኛይቱ ቤተ ክርስቲያን እናየዋለን፡ እግዚአብሄር እንደተናገረው፡ በኤልያስ ዘመን፡ ኤልዛቤል ልጆቹን ስታንበረክክም እንዲሁ ፈቅደውላት ነበር። አሁንም ጴንጤቆስጤ ያለችበትን ተመልከቱ። ማይ፡ ማይ! በቃ ተነቃቀለች። እና ለአንድ ሺህ ዓመታት ያህል፡ ከ... 500 እስከ 1500፡ በትክክል፡ ያም 606 እስከ 530ʹዎቹ... 520፡ ትክክለኛ ቁጥሩ ያ ነው፡ ነገር ግን አንድ ሺህ አመታት። ደም አፍሳሽ መከራዎች... አደረጉበት። ታሪክ አንብቡ።

47 አሁን፡ አንድ ካቶሊክ ሰው ስለ ክርስቲያን ቤተክርስቲያን፡ የክርስቲያን ቤተክርስቲያን እና ነን ይላችኋል። እነርሱ የክርስትያን **የኃይማኖት ተቋም** ናቸው። እውነተኛ ጴንጤቆስጤዎች ግን በመጣበብ ሰደት፡ ተገድለው፡ በጳጳሳት እና በኤጲስቆጶሳት ለሞት እና ለልዩ ልዩ ነገር ተዳርገው፡ እየተገደሉ፡ ከመጠን ያለፈ ደማዊ ነበረ።

48 እንግዲህ፡ ተመልከቱ፡ ይህን በማለቴ፡ አንድ ቀን ህይወቴን ያስከፍለኛል። ያ ግን እርግጠኛ የሆነ ነገር ነው፡ በየትኛው መንገድ እንደምሄድ አውቃለሁ፡ አሁን አውቃለሁ። በደም መንጠባጠብ ይቀጥላል። ሰዓቱ ግን አሁን እየደረሰ ነው፡ አሁን በሀገሪቱ ውስጥ በምታዩት ሁኔታ መሰረት ብዙ የሚቆይ አይደለም። ፈጽማችሁ አትተማመኑበት! እውነቱ ይህ ነው። በቅንነት ጸንታችሁ ያዙ። ያኔ በእነርሱ ላይ እንደተፈጸመ እናንተንም ደማችሁን ቀላቅሉበት።

49 እንግዲህ፡ እዚህ ጋር ምን እንደተፈጠረ አይታችኋል። ከዚያም እዚህ የኤልዛቤል ትምህርት ገባ። ኤልዛቤል ሴት ነበረች፡ አረማዊት ሴት... አክዓብም ቆስጠንጢኖስ ያደረገው ተመሳሳይ ነገር አደረገ፡ መንግሥቱን ያጸና ዘንድ ይህችን ሴት አገባ፡ ቆስጠንጢኖስ ያኔ እንዳደረገው ጣዖት አምልኮን ወደ እስራኤል አመጣ። በዚህም ጴንጤቆስጤ ሙሉ በሙሉ በመጥፋት ደረጃ ላይ ደረሰ።

50 ያኔ፡ እግዚአብሔር ማርቲን ሉተርን አስነሣ። **እዚህ** ጋር እንዴት እንደወጣ እና እንዴት ሙሉ በሙሉ እንደደበዘዘ ልብ እንድትሉ እፈልጋለሁ፡ ከዚያም **እዚህ** ይጀምራል፡ እንደገናም **ወደዚህ** ይወርዳል። እና እንደ ጌታ ፈቃድ፡ ይህ ነገር ለእሁድ ምሽት ታላቅ ትምህርት ስለሆነ—በዚህ ላይ ምልክት አድርጌበታለሁ።

51 አሁን—እንግዲህ፡ ወደ መዳረሻችን አቅጣጫ መንገዳችን ይዘናል ብዬ አምናለሁ። ስለዚህ፡ በዚህች ዘንድ፡ **እዚህ** ጋር—የጨለማው ዘመን አለ፡ ይህም ከ 1500... ከ 606 እስከ 1520 ይደርሳል። እዚህኛው ጋር። በደንብ እንድትይዙት እዚህ ጋር አደርገዋለሁ... 606 እስከ 1520። ይህ ማለት የጨለማ ዘመን ነው፡ **ይህችኛዋ** ቤተ ክርስቲያን፡ የጨለማ ዘመን ናት። ስለዚህ፡ አሁን እየወጣንባት ያለነው ቤተክርስቲያን የሉተራን ቤተ ክርስቲያን ናት።

52 እንግዲህ፡ በዚያ ውስጥ የነበረው አብዛኛው ሰው፡ እነዚያ ሰዎች ሁሉ አልቀዋል... እነዚህ ሰዎች እነ ኢራኔዎስ፡ ማርቲን፡ እና ኮሉምባ፡ እና እነዚህ ሁሉ ደብዝዘዋል። አሁን እውነተኛ ታሪክ ብቻ ይሁን፡ የፈለጋችሁትን ታሪክ ወደ ኋላ መመርመር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አምጡ፡ “ቅዱስ ፓትሪክ ካቶሊክ

ነበር" ብለው ሊነግሯችሁ ከፈለጉ፡ ሰለምን እንደሚናገሩ የማያውቁ ናቸው። ቅዱስ ፓትሪክ ግን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ተቃዋሚ ነበረ፡ ወደ ሮም ሄዶ አያውቅም፡ ትምህርታቸውንም አጥብቆ የሚጠላ ነው። በትክክል እውነት ነው። ወደ ሰሜን ኢንግላንድ-... ወይም የዛሬዋ አየርላንድ ብትሄዱ፡ ተመሳሳይ ነገር ታያላችሁ። ቅዱስ ፓትሪክ የእግዚአብሔር ሰው ነበር! ሰለ ቅዱስ ፓትሪክ፡ ግን፡ እባቦችን ሁሉ ከአየርላን—አባረራቸው ብለው ሲናገሩ፡ ያ አፈ ታሪክ ነው።

53 ዊልያም ቴል ወርውሮ ከልጁ ጭንቅላት ላይ ፖም አወረደ ሲባል ሰንቶች ሰምታችኋል? ያ የካቶሊክ አፈ ታሪክ ነው፡ በጭራሽ እንደዚህ አይነት ቃል አልነበረም። ይህ ተፈጸመ የተባለበት ቦታ በአካል ሄጃለሁ። "አፈ ታሪኩ፡ እንደዚያ አይደለም፡" የተጻፈው፡ በሰዊዘርላንድ ነው። እኔና ቢሊ ይህ ነገር ተፈጸመ በተባለበት—ወርውሮ ሰው የመታበት፡ በሉሴርን ሀይቅ ዳር ቆመን አይተነዋል፡ አዎን ሰውን መቷል፡ ከልጁ ራስ አፕል ግን አይደለም። ያ አፈ ታሪክ፡ አጉል እምነቶች፡ እና ያልነበሩ ነገሮች ናቸው። በዚያ መፈጸሙ ወይ የተፈጸመበት ቦታ እንኳ፡ የሚያውቁት ነገር የለም፡ እንዲህ ብሎ ነገር የለም። እና በእውነቱ የዚህ ነገር ምንነት እሷም የሚጥላት ነገር በትክክል ያሰረዳል። በዚህ ውስጥ፡ ግን፡ እሱ ሰራው የሚሉትን በእውነቱ ታሪክ አይደለም። ተመልከቱት።

54 ሰለዚህ አሁን እዚህ፡ በቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ከህልውና ውጪ የሆነው፡ እና የደበዘዘው በዚህ ነው። አሁንም በዚህ በሌላኛው ዘመን የተሃድሶ ዘመን መጣ። ሰለዚህ፡ እነዚህ ነገሮች ከአንድ ሺህ የመጥቆር እና የጨለማ እና የመደብዘዝ አመታት ገደማ በኋላ፡ እና ከተለያዩ ነገሮች በኋላ፡ ቤተ ክርስቲያን ከኢሬኔዎሰ እይታ ወደ መጥፋት ደረሰች። እሱ ታላቅ፡ እና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ሰው ነበር። በመቶዎች የሚቆጠሩ የከበሩ ቅዱሳንም በቻሉት መጠን (በዚያ ሜዳ ቆመው) ደማቸው በነጻ በመሰጠት እንዲሁ ነበሩ፡ ይህም፡ ሰለ ክርሰቶስ፡ በኢየሱስ ክርሰቶስ ሰም ሰለ መጠመቅ፡ በልሳኖች ሰለ መናገር፡ ሰለ ኢየሱስ ክርሰቶስ ህይወት እራሳቸውን ክርሰትያኖችን ነን፡ ብለው **በሚጠሩ** ሰዎች እየተሰደዱ በትንሳኤው ህይወቱ እና በመለኮታዊ ህልውናው ይኖሩ ነበር። ይህ እውነት ነው። በትክክል።

55 አቤት፡ እንደው—ገሃንም-የሚገባቸው አጋንንታውያን ሌጌዎኖች እንጃ-እኔ-በቃ-አላውቅም። እንዲሁ መጡና እራሳቸውን አደራጅተው እና አቀናጅተው፡ "እራሷን ነቢይት ነኝ፡ የቃሉን ብቸኛ መለኮታዊ ተርጓሚ፡ ከእኛ በቀር ማንም አያውቀውም አሉ።" እራሷን ነኝ ትላለች እንጂ፡ ውሸታም ነች። አያችሁ? ይኸው ነው። እርሱ ግን በተመሳሳይ ጊዜ፡ እውነትን አሰጨብጦ፡ መልእኩን ወደዚያ ላከ። እውነት ሁልጊዜ ወደዚህ ይመለሳል። አያችሁ? እውነት ሁሌም ወደ ዋናው ይመለሳል፡ ምክንያቱ እግዚአብሔር በነገር ሁሉ አይለወጥም።

56 አሁን፡ በልባችሁ ውሰጥ ይቀመጥ ዘንድ፡ ከዚህ ሳንወጣ፡ ትናንት ማታ፡ ያየነው ነገር አለ። ኤልዛቤልን፡ በጥላ ብቻ... ሳይሆን፡ ሴት ልጅ—እንደነበረቻትም አይተናል። ትዝ ይላችኋል? በራእይ 13 በተጨማሪ ከሃዲዋ ቤተክርስቲያን፡ ማለት ሮም፡ ሴት ልጆች ነበሯት ይላል። "የጋለሞታዎች እናት ነበረች።" እውነት ነው ወይ? ኤልዛቤል ሴት ልጅ ነበራት፡ ኤልዛቤልስ በልጇ ላይ ምን አደረገች? እነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች እና ጥላዎች፡ እንዴት እንደሆኑ አይታችኋል። ኤልዛቤል ሴት ልጅዋ በይሁዳ የሚኖረውን፡ የኢዮሣፍጥን ልጅ ኢዮራምን እንዳገባች እየች።

57 በወቅቱ፡ እስራኤል እንዲህ ተከፋፍላ ነበር። ኢየሩሳሌም **ወደህ**፡ ይሁዳም **ወዲያ** ነበሩ። እነሆ፡ አክዓብ **በዚህ** ነበር፡ ኢዮራምም **በዚያ** ነበር። ልብ በሉ፡ ኤልዛቤል **ይህን** ድል አድርጋ፡ እስራኤላውያን ሁሉ በጣዖታት ሞላች። ከዚያም... (ከኤልያስ እና ከታናሽ መንጋው በስተቀር ሁሉንም እሷን ተከተሉ።) እሺ። አሁን፡ **በዚህ** በኩል ኢዮራም በይሁዳ ላይ ነበረ፡ ከአክዓብም ልጅ በወለደች ጊዜ፡ ልጇን ወሰዳ ለኢዮራም ልጅ ዳረቻት... ማለት ለኢዮሳፍጥ ልጅ ለኢዮራም፡ ወደ ይሁዳም ጣዖታት አመጣች፡ በኢየሩሳሌምም የረማውያን መሠዊያዎች አቆመች።

58 የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ያደረገችው ይህንኑ ነው! የኃይማኖት ተቋም እና የልዩ ልዩ አስተምህሮቶቿ አጥብቃ ያዘችና፡ ከሴት ልጇ ጋር በመተባበር **እነሆ** መንፈስ ቅዱስን ከቤተክርስቲያን አስወገደች (ሉተራን፡ ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ጴንጤቆስጤ፡ እና የመሳሰሉት)። በትክክል ያደረገችው ያ ነው። መጽሀፍ ሲናገር "የጋለሞታዎች እናት ነች፡" ይላታል።

59 አሁን፡ ቃሉን ብቻ ተመልከቱት። ይሄውላችሁ—በእግዚአብሔር ቃል ላይ እና በታሪክ ላይ ከዚህ በተለየ መልኩ፡ በደንብ የሚያሳይ ነገር ካያችሁ፡ በጨዋነት ወደ እኔ ኑ። አያችሁ? በትክክል። የለም አታገኙም!

60 እነዚህ የሃይማኖት ተቋማት በፕሮቴስታንት እምነቶች ከገጠሙን መርዛማ ነገሮች ዋናዎቹ ናቸው፡ እነዚህም ቤተ ክርስቲያንን በሰዎች እንድትመራ እንዲመሩ ይጥራሉ፡ በዚያ በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጠ ሌላ ምስል ለማስቀመጥ ነው። የጴንጤቆስጤዎች የበላይ ጠባቂ፡ የቢሾፖች አለቃ፡ "እስኪ፡ አሁን፡ አስተምህሮቱ አሳዩኝ፡ ምን አይነት ነው? ኧረ፡ በኢየሱስ ሰም አጥማቂ ነው እንዴ? ወደዚህ መግባት አይችልም። አይችልም፡ ወዳጆች፡ ወንድሞች ሆይ። ቀዳችሁ ጣሉት።" ይህም ተቀዶ መጣል ያለበት ነው። "ይህን እንድትገነዘቡ አሳስባችኋለሁ፡ ማናችሁም ወደዚያ ሰብሰባ እንዳትሄዱ። አስጠሊታ ነው። የቱንም ያህል ብትታመሙ፡ የቱንም ያህል እግዚአብሔር ይሰራበት፡ ከዚያ ራቁ። በእኛ መነጽር ማየት ካልቻላችሁ፡ በቃ፡ ታውራችኋል።" ለአውሬው ምስል አደረጉ! ምስሉም ህይወት አለው ይናገራል። ይህ በትክክል ትክክለኛ ነው። መናገር አይችልም ብላችሁ ካሰባችሁ፡ ሂዱና እሱን ለማታለል ሞክሩ። ኧሃ-ሃህ፡ በትክክል መከራ ውስጥ ትገባላችሁ።

61 በቱልሳ፡ ኦክላሆማ፡ የገጠመኝን፡ አስታውሳለሁ... እነሆ፡ በጣም በሚያስጠላ አጋጣሚ ውስጥ ነበርኩና፡ የኃይማኖት ተቋማት በሙሉ እየተርመሰመሱ ነበር። እናም አንድ ቀን በዚህ ህንፃ ውስጥ ቁጭ ብዬ አንድ ራእይ—አየሁ። አንዲት—ሚጢጢ... ቆንጆ፡ ድመት አየሁ፡ እና በሐር ትራስ ላይ ጋደም ብሎ አየሁት፡ እጅግ የሚያምር ነበር። ወደሱ አቅጣጫ ጠጋ አልኩኝ (እና እኔ ድመቶችን እፈራለሁ)፡ እኔም ሄጄ እሱን መነካካት ጀመርኩ፡ እና "ፑር፡ ፑር፡" እያለ ይሄዳል። የሚያወጡትን ለየት ያለ ድምጽ፡ ታውቁታላችሁ። "አንተ ቆንጆ፡ ሚጢጢ ድመት፡" እያልኩት፡ መነካካቴን ቀጠልኩ። እርሱም፡ ልክ እንደ፡ ጥሩ ነገር "ፑር፡" ይላል።

62 እናም ከትራሱ ጀርባ፡ "የጴንጤቆስጤ ድመት፡" የሚል የተጻፈበት ጽሑፍ አየሁ። አሰብኩትና፡ እንዴ፡ "ይህ ራዕይ መሆን አለበት።" "እንግዲህ፡ ይህ እንግዳ ነገር ነው፡" አልኩኝ።

63 እና የሆነ ነገር እንዲህ አለኝ፡ “ጸጉሩን በዚህ መልኩ እስከነካካኸው ድረስ፡ ሁሉ ደህና ነው፡ አሁን ግን ተፈጥሮውን በትክክል ማወቅ ከፈለግክ፡ ጸጉሩን ከበስተኋላው በኩል ንካው።” አያችሁ? እናም ፀጉሩን ወደ ኋላ ሰነካው፡ አረንጓዴ ዓይኖች፡ አጉሮጥርጦ አወጣቸው፡ እና የቻለውን ያህል እየተፋብኝ አደገኛ አውሬ ሆኖ ከፊቴ ቆመ። አያችሁ፡ እስኪ ከወደኋላው በኩል ጸጉሩን ነካ አርጉት። እስኪ ንገሩት “የአብ፡ የወልድ፡ እና የመንፈስ ቅዱስ” ጥምቀትህ የዲያብሎስ እና የካቶሊክ ቤተክርስትያን ነው በሉት፡ ያኔ ምን እንደሚሆን እዩት። አያችሁ? ጸጉሩ ይቆማል።

64 ከዚያም ወርጄ፡ ለወንድም ጂን እና በዚያ ለነበሩ… ለሌሎች፡ እነ፡ ወንድም ሌዮ እና ሌሎች፡ እንዲህ አልኳቸው፡ “ስለ ጴንጤቆስጤ ኃይማኖት ተቋም ጥርት ያለ ራእይ አይቻለሁ።”

65 አሁን ወደ 3ኛ ምዕራፍ፡ ከሁሉ በፊት… ሰርዴስ የሞተች ቤተ ክርስቲያን ናት። በዚህ ጊዜ ውስጥ ስለተገደሉ ሞተዋል። ትንሹ የህይወት ዘመን፡ ምን እንደነበረ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ እናገኘዋለን። ከ1520 እስከ 1750 ይህ የሰርዴስ ዘመን ነበር። ኮከቡ፡ ወይም መልእኩ… ማለት በእጁ የነበረው ኮከብ፡ እርሱም የዛ ቤተ ክርስቲያን ዘመን መልአክ ወይም መልእክተኛ ነበረ። ይህ በግልጽ ተረድተነዋል አይደል? ኮከቡ መልአክ ነው፡ መልአክም የዚያ ዘመን መልእክተኛ ነው። በጣም ጥሩ። በጣም ጥሩ።

66 አሁን ስለ ኒቂያ ጉባኤ ጨርሰነዋል። እሷም በዚያ ሞተች፡ ሁሉም ወደ ስልጣን እና ወደ ክብር መጡ፡ ቤተክርስቲያን እና መንግስት አንድ ሆነዋል። እና የትናንትናውን ትምህርት የሚያስታውስ ሰው አለ፡ ብዙ ሰዎች የመሰላቸው ምን ነበር? “የሺ አመት መንግስት የገባ መሰላቸው።” ሁሉም… “ያለ ክርስቶስ መምጣት የሺ አመት መንግስትን ማምጣት አሰቡ።” አያችሁ? በመጀመሪያ ነገር፡ የሺው አመት መንግስት የሚያመጣው የክርስቶስ መምጣት ነው። እና በዚያ ዘመን የነበራቸው ነገር… ታሪክን ከወሰዳችሁ፡ በጊዜው የተነሱ ሐሰተኛ ኢየሱሶች እና ልዩ ልዩ ነገሮች እንደነበራቸው፡ ታያላችሁ። እንዲያውም ጳጳሱን፡ “በእግዚአብሔር ልጅ ፈንታ” **ምሰሌኔ** ብለው ሲጠሩት፡ ኢየሱስ ነው ብለው አሰበውት ነበር። አዎን፡ ቁጭ ያለ፡ አይነት፡ ግዙፍና ቅዱስ አምላክ አረጉት።

67 አንድ ነገር ልንገራችሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ሲመጣ… ከመምጣቱ በፊት ይላል፡ “ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉ፡ ሐሰተኛ ኢየሱሰም ይነሣሉ።” በትክክል። “እነሆ፡ እዚህ… ” ግን ይህንን ወደ ልባችሁ ልወርውር፡ ቤተክርስቲያን እስክትነጠቅና እስክትወሰድ ድረስ በዚህ ምድር ላይ እግሩን የሚረግጥ ኢየሱስ አይኖርም። እንግዲህ፡ ይህን በልባችሁ ያዙ፡ ምክንያቱ ሐሰተኞች ክርስቶሶች ይነሳሉ። ኢየሱስ ግን ምድርን በጭራሽ አይረግጥም፡ መለከት ይነፋልና፡ እናም አየር ላይ እናገኘዋለን እንጂ፡ በጭራሽ አይመጣም። ቤተክርስቲያን ሄዳለች። ከዚያም ኢየሱስ የሚገለጠው፡ በመመለሻው ጊዜ ይሆናል። አሕዛብ በአየር ሊቀበሉት ሄደዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ነው አይደል? አያችሁ? በአየር ላይ ሊገናኙት ይሄዳሉ፡ ከዚያም ወደ ላይ እንወጣለን። ኢየሱሰም… ቤተክርስቲያን እስክትነጠቅ እና ወደቤት እስክትሄድ ድረስ የሰርጉ እራት በሰማይ እስኪፈጸም ድረስ እግሩ ምድርን በጭራሽ አይረግጥም፡ ያኔ ከአይሁድ ቅሪት በኋላ ተመልሶ ይመጣል።

68 ስለዚህ፡ አሁን፡ የኒቂያው ጉባኤ ተጠናቋል። ቤተ ክርስቲያን—በጳጳሱ አገዛዝ ሥር ለሺህ ዓመታት ያህል ቆይታለች። ከእነሱ ጋር የማይስማሙትን ሁሉ ገድለዋል። ትክክል። ከአገዛዛቸው ስር ካልወደቃችሁ፡ ኤልዛቤል በእስራኤል ላይ እንደፈጸመችው እናንተም—ት—ትገደላላችሁ።

69 በዚያን ዘመን ጉልበታቸውን ለበልዓም ካላንበረከኩ ጥቂት የእስራኤል ቅሪቶች፡ እና ከኤልያስ በቀር መንፈስ ቅዱስ በሙላት ከሁሉም በአንድነት ሸሽቶ ነበር። ያንን ለማንበብ ከፈለጋችሁ፡ አንደኛ ነገሥት፡ ምዕራፍ 19፡ ከቁጥር 18 ላይ ነው፡ ኤልያስም በዋሻው ውስጥ ቆሞ እንዲህ አለ፡ “ጌታ ሆይ፡ ነቢያትህን ሁሉ—ገድለዋል። ህሁሉንም ነገር ፈጽመዋል፡ እነሆ እኔም—ብቻዬን ቀርቻለሁ። ያመለጥሁት እኔ ብቻ ነኝ።” እግዚአብሔር ግን ጉልበታቸውን ለበኣል ያላንበረከኩ፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ምእመናን እንዳሉት ነገረው።

70 ስለዚህ አሁን፡ ሰርዴስን፡ እንጀምራለን። **ሰርዴስ** የሚለው ቃል፡ 1ኛ ቁጥር ላይ። **ሰርዴስ** የሚለው ቃል፡ በእንግሊዘኛ አገላለጽ፡ ትርጉሙ፡ ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ “ያመለጡ” ማለት ነው። እውነተኛው **ሰርዴስ** “ያመለጡ” ነው። **ሰርዴስ** ማለት ያ ነው፡ እሺ፡ “ያመለጡ።” አሁን፡ እዩት፡ “ያመለጡ” ነው።

71 አሁን በ 1ኛ ላይ እንጀምራለን። **የተሃድሶ ዘመን** በማለት እንጠራዋለን… በጣም እና እንዲህ ብለን ቢኖርብንም እጅግ የሚመጥነው ሰያሜ ነው፡ ምክንያቱ… ተሐድሶው ራሱ “ያመለጡት” ከዚያ አምልጠው ስለወጡ የሚመለከት ነው።

72 አሁን 1ኛውን ቁጥር እንወስዳለን፡

> **… ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡ ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት** እና**… ሰባቱ ከዋክብት ያለው፡ እንዲህ ይላል፡** *ሥራህን* **አውቃለሁ፡ ሕያው እንደ መሆንህ ስም** አለህ፡ **ሞተህማል።**

73 አሁን ሰላምታው። እንግዲህ፡ ሰባቱ መናፍስት ማለት… “ሰባቱ መናፍስትና ሰባቱ ከዋክብት።” እነዚህ መናፍስት ወደ መልእክተኞቹ ከዋክብት ወደ ሆኑ የሄዱ መላእክት ናቸው። “ሰባት መናፍስት፡” መንፈስ ቅዱስ ሰባት ጊዜ መልእክተኛ ይቀባል፡ ይህም ለዘመኑ ለተላከው ለእያንዳንዱ ኮከብ ነው። መንፈስ ዘ—ላለማዊ ነው፡ እና በጨለመው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ላይ ብርሃን እንዲያንጸባርቅ የተሰራው ኮከብ ሻማዎች እና ከዋክብትን የሚወክሉ ናቸው። መልአኩ፡ መንፈሱ፡ በዚህ ኮከብ አማካኝነት ለዚያች ቤተ ክርስቲያን ዘመን ብርሃን እንዲያንጸባርቅ ወደ ኮከቡ የሚሄደው ይህ ነው። እናንተም፡ ሰባቱ መናፍስት… ምንድናቸው ብላችሁ ትደነቁ ይሆናል። የሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ሰባት መልእክተኞች ናቸው። አያችሁ? ስለዚህ፡ ይህ ኮከብ ወደዚህ ወደ አገልግሎቱ በወጣ ቁጥር፡ መንፈስ ቅዱስም ወርዶ ያንን ኮከብ ልክ እንደፊተኛው ቅባት አድርጎ ይቀባዋል።

74 አሁን ይህን ለእናንተ እንዳረጋግጥላችሁ—ፍቀዱልኝ። ጳውሎስ፡ ምን አይነት ኮከብ እንደነበረ ማወቅ ካለባችሁ ብሏል። ምክንያቱ፡ ሰይጣንም፡ ኮከብ እንደሆነ፡ አስታውሱ፡ የንጋት ኮከብ ነው። አሁን አስተውሉ፡ ጳውሎስ እንዲህ አለ… እሱ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ኮከብ እንደነበረ ታምናላችሁ?

እንዲህ አለ፡ እንግዲህ፡ እውነት መሆኑ እና አለመሆኑ ማወቅ ከፈለጋችሁ። በገላትያ 1፡8 ላይ፡ ጳውሎስ ሲናገር፡ እንዲህ አለ፡ ከጊዜ በኋላ ጨካኞችም ተኩላዎች፡ የሚመጡበት ግዜ ይኖራል፡ እንዲህ አለ፡ “መልአክም ቢሆን ከሰማይ ወርዶ ሌላ ወንጌልን ቢያስተምር... ” (እንግዲህ፡ ይህ መልአክ መስሎ የሚመጣውን **ምትክ** እየመጣ እንደሆነ አስቀድሞ አውቋል።) እንዲህ አለ፡ “ማንም ይሁን፡ መልአክም ሌላም ይሁን መጥቶ እኛ ካስተማርናችሁ ወንጌል የሚለይ ቢያስተምር፡ የተረገመ ይሁን።” ልክ ነው?

75 በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ካልተጠመቁ እንደገና እንዲጠመቁ ያስገደዳቸው ጳውሎስ ነው፡ “መንፈስ ቅዱስን እንድትቀበሉ ኑና እንደ ገና ተጠመቁ፡” የሐዋርያት ሥራ 19፡5። ደግሞም በሕዝቡ ላይ እጁን የጫነ እርሱ ነበር፡ ስጦታዎች እና፡ ተአምራትን በማድረግ፡ በመለኮታዊ ፈውስ፡ ልሳን መናገር፡ ልሳን በመተርጐም ላይ ቤተ ክርስቲያንን በሥርዓት ያደራጀ እርሱ ነው። ልክ ነው? በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡ ጳውሎስ የተናገረውን ተመልከቱ። አንደኛ ቆሮንቶስ 12 ላይ፡ ታገኙታላችሁ። በቤተክርስቲያን ውስጥ አደራጀ... እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እነዚህን ታላላቅ ስጦታዎች አስቀመጠ፡ ጳውሎስም ለእግዚአብሔር ክብር ይሠሩ ዘንድ፡ አቀናጅቶ አደራጃቸው። ጳውሎስ እንዲሁ ተናግሯል። ስለዚህ የየትኛውም ኀይማኖት ተቋም ተከታይ፡ የሆነ ማንም ቢሆንም፡ በልሳኖች የመናገር፡ በልሳኖችም የተነገሩትን የመተርጎም እና መለኮታዊ ፈውስ፡ ተአምራቶች፡ እና የመንፈስ ቅዱስ የጥምቀት ምስክር፡ አልፏል ሊላችሁ የሚሞክር ማንም ሰው... የተረገመ ይሁን። በጳውሎስ ላይ የነበረው ያው መንፈስ ወደ ቀጣዩ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ከዚያም ለቀጣይዋ የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ተመሳሳይ መንፈስ ነው፡ እስከ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ፍጻሜ ድረስ የሚላከው ያው መንፈስ ይሆናል። ያው መንፈስ፡ መንፈስ ቅዱስ። ይህን ታምናላችሁ?

76 ይህን ካስተዋላችሁት፡ እዚህ ጋር የተጻፈ ነው። ጸሐፊው ያውቀዋል። “ሰባቱ መናፍስት፡” ተመልከቱ። መንፈስ ቅዱስ ሲል፡ አንደኛው ብቸኛው፡ ትልቁ “ኤስ፡” እንደሆነ ተመልከቱ። ኧሃ-ሃህ። ያው መንፈስ ቅዱስ ለሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት አንድ ዓይነት ብርሃን ይዞ ሰባት ጊዜ ይመጣል። አሁንስ ገብቷችኋል? ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት፡ ይህ መንፈስ ቅዱስ ይህን ተመሳሳይ መልእክት ሰባት ጊዜ ያመጣዋል! ለሚለውጠው ሰው ሁሉ እርግማን ያስተላልፋል።

77 አሁን የነገሩ መገለጥ ሁሉ ከዚህ ጋር የሚጣጣም ከሆነ እዩት። “አንዳች የሚያጎድል ወይም የሚጨምር፡ (ዕድሉ) ከህይወት መዝገብ ይጎድልበታል፡” አለ። ነገሩ ሁሉ የተዘጋው በዚህ መንገድ ነው። አያችሁ፡ ነገሩ ይህ ስለሆነ፡ የምትዘሉት ወይም የምታጣብቡት ሌላ ስፍራ የለም። ያ ነው እግዚአብሔር የተናገረው፡ መንፈስ የተናገረው ያ ነው፡ አብያተ ክርስቲያናት የተናገሩትም ያ ነው። ስለዚህ፡ ጳውሎስ ካስተማረው ትምህርት ውጪ ማንኛውም አይነት ትምህርት ለማስገባት ከሞከራችሁ፡ ስህተት ነው! መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል ነው። ዕድሉን... “ዕድሉን ከሕይወት መጽሐፍ ውስጥ አጎድላለሁ፡” ብሏል ኢየሱስ።

78 እናንተም፡ እንዲህ ትሉ ይሆናል፡ “የትኛው የሕይወት መጽሐፍ ክፍል? ”

79 ስማቸው በህይወት መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎላቸው የነበሩ መጨረሻቸው ውድቀት የሆኑ ብዙዎች አሉ። ይህን ታውቃላችሁ፡ አይደል? የበቀደም ማታ ትምህርት ታስታውሱታላችሁ? ገብቷችኋል? እንደገና ተመለሱበት፡ ጥሩ ነኝ አትበሉ፡ ልክ ነኝ አትበሉ፡ አያችሁ።

80 የአስቆሮቱ ይሁዳም የሰይጣን ልጅ ነበረ፡ በሥጋ የተገለጠ ሰይጣን ነበር። መጽሐፍ ቅዱስም ይመሰክራል። "የጥፋት ልጅ ሆኖ እንደተወለደ፡" መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል።

81 ለአፍታ ያህል ይህን እዩት። እና፡ **በዚህ** በኩል ኢየሱስ ነበር፡ **እዚህ** በቀኝ በኩል ሌባ ነበር፡ ሌላውም **እዚህ** ጋር በግራው ነበረ። አሁን፡ ኢየሱስ... የእግዚአብሔር ልጅ ነበር። ልክ ነው ወይ? አሁን ሰዎች፡ ሶስት መስቀሎችን ብቻ ያያሉ፡ ነገር ግን አራት ነበሩ። አራት መስቀሎች! እሺ፡ መስቀል ምንድን ነው? ዛፍ ነው። ልክ ነው? መጽሐፍ ቅዱስም "ዛፍ ላይ የሚሰቀል ርጉም ይሁን።" ይላል። እርሱ ዛፍ ላይ ተሰቅሎ፡ ስለ እኛ መርገም ሆነ። ስለ ተቆረጠ እንጂ፡ ዛፍ የነበረ ነው። ልክ ነው ወይ? በጣም ጥሩ። **እነሆ** እዚያ፡ ከኮረብታው ግርጌ፡ ሌላ ቆሟል። ይሁዳ ራሱን በሾላ ዛፍ ላይ ሰቅሏል። ልክ ነው?

82 ተመልከቱ! **እነሆ** ከሰማይ የወረደው የእግዚአብሔር ልጅ፡ ንስሐ የገባውን ኃጢአተኛም ከእርሱ ጋር፡ ወደ መንግሥተ ሰማይ፡ እየተመለሰ ነው። **እነሆ** ከሲኦል የመጣው፡ የጥፋት ልጅ፡ ንስሓ ያልገባውን ሐጢአተኛውን ይዞ፡ ("አንተ ከሆንክ!") ወደ ሲኦል እየተመለሰ ነው። ንስሐ ያልገባ ኃጢአተኛ፡ እዩት፡ "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፡ ራስህንም እኛንም አድን።"

83 **ይሄኛው** ግን እንዲህ ይላል፡ "እኛስ... " (ወንጌል ሰባኪውን፡ ሰበከው) "እኛስ የሚገባንን ተቀብለናል፡ ይህ ሰው ግን ምንም አልበደለም። ጌታ ሆይ፡ በመንግስትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ።" ያ ምን ነበር?

84 ባለፈው ምሽት ወይም ከዚያ በፊት በጥቂቱ አይተነው... ?... ነበር። **ይህ** የእግዚአብሔር አቤል ነው፡ **ያም** የዲያብሎስ ቃየን ነው። ቃየን አቤልን በመሠዊያው ላይ እንደገደለው፡ ይሁዳም ኢየሱስን በመሠዊያው ላይ ገደለው። በትክክል። **ያኔ** በኤደን ገነት የወጣው ጭስ እነሆ እንደገና **እዚህ** ጋር ወረደ። ይህ በትክክል እውነት ነው።

85 ኦህ፡ የከበረው፡ የጥንቱ መንገድ፡ የተባረከው የጥንቱ መንገድ፡ በክብር የተሞላ!

86 አሁን፡ አሁን እዚህ የምናገኘው (ይቅርታ።) ይህች የሰርዴስ ቤት ክርስቲያን፡ መልአኩን፡ "ሰባቱ መናፍስት፡ ሰባቱ መንፈሶች ያሉት፡" ይለዋል።

**... ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡ ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ያሉት እንዲህ ይላል፡...**

87 እስኪ አሁን እግዚአብሔር አንድ መንፈስ መሆኑን የምታውቁ ሰንቶች ናችሁ? በእርግጠኝነት። መንፈስ ቅዱስ የሆነው፡ እግዚአብሔር። አብ፡ መንፈስ ቅዱስ የሆነው፡ እግዚአብሔር፡ አንድ አካል ነው፡ ምክንያቱም ማርያም ከመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኝታለች። አሁን፡ ግን... እግዚአብሔር ይህ መንፈስ ቅዱስን ለሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት፡ በሰባት የተለያዩ የወንጌል ብርሃናት ለቤተክርስቲያን ተጠቀመበት። ገብቷችኋል? ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት።

88 እንግዲህ፡ እናንተም “እግዚአብሔር እንዲህ አያደርግም፡” ትላላችሁ። ኧረ፡ ያደርጋል፡ ወንድሜ።

89 ተመልከቱ! የኤልያስን መንፈስ ተጠቀመበት፡ ኤልያስ ከሄደ በኋላም... ኤልያስ ካለፈ በኋላ፡ ኤልሳዕ የእርሱን ሁለት እጥፍ ተቀበለ። ኤልሳዕም ታሞ በሞተ ጊዜም፡ በመጥምቁ ዮሐንስ ላይ እንደ ገና መጣ። ኤልያስ ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ፡ ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርግ አደረገው፡ በምድረ በዳም ኖረ። ልክ ነው ወይ? እና በመጨረሻዎቹ ቀኖች እንደገና እንደሚመጣ ትንቢት ተናገረ፡ አያችሁ። እግዚአብሔር መንፈሱን በተደጋጋሚ ይጠቀምበታል።

90 ኢየሱስም በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶ፡ መልካም እያደረገ ዞረ። ልክ ነው? በኢየሱስ ላይ የነበረ ያን መንፈስ ቅዱስም፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመልሶ መጣ፡ ወደ ቀጣዩ ዘመን ተመልሶ መጣ፡ ወደ ቀጣይ ዘመን፡ ወደ ቀጣይ ዘመን። ይህ ማን ነው? ያው እና አንዱ-ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው። ኦህ፡ አይታያችሁም ወይ? አብ፡ እግዚአብሔር ከእኛ በላይ ነው፡ ወልድ፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፡ መንፈስ ቅዱስም፡ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ነው። ሶስት መገለጫዎች እንጂ፡ ሶስት አማልክት አይደሉም። አያችሁ? እነዚያም ሦስቱ የማዕረግ ስሞች (አብ፡ ወልድ፡ እና መንፈስ ቅዱስ) የአንድ ስም ናቸው፡ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በጣም ጥሩ።

91 አሁን፡ እንቀጥላለን ተከታተሉ። “ሰባቱ መናፍስት፡” ይላል በእጁ የያዛቸው... በሌላ አባባል፡ “መልክተኞቹን የያዛቸው።” በመንፈስ ቅዱስ የሚቀቡ መልእክተኞች፡ ጳውሎስ (በመጀመሪያው) በተቀባበት በዚሁ መንፈስ ቅዱስ፡ ሁለተኛው፡ ሦስተኛው፡ አራተኛው፡ አምስተኛው፡ ስድስተኛው፡ ሰባተኛው፡ ሁሉም በቀኝ እጁ ይቀባሉ። ኦህ፡ ኃይላቸውንና ብርሃናቸውን ከቀኝ እጁ ያገኛሉ።

92 ከዚያ፡ ወደ ሰማይ ዐረገ። ፍሊጶስ ሲሞት፡ እንዲህ ብሎ ተናገረ... ማለቴ እስጢፋኖስ እንዲህ አለ፡ “ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ፡ እና... ሰማያት ተከፍተው አያለሁ።” ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር ታላቅ ቀኝ እጁን ኖሮት እርሱ ላይ ቆመ ማለት አይደለም፡ **ቀኝ እጅ** ማለት ግን “የኃይል እና የሥልጣን” ቀኝ እጅ ማለት ነው።

93 እግዚአብሔር የፈጠረው ያ አካል... “ቅዱሴ መበስበስን ያይ ዘንድ አልፈቅድም፡ ነፍሱንም ሲኦል ውስጥ አልተወውም፡ አስነሳዋለሁ በመንፈሱ ፈንታ መሰውያው ላይ አደርገዋለሁ።” ተመልከቱ! መሰውያው ላይ ሲያዩት—— ቁጭ ብሎ፡ መጽሐፍንም በእጁ ላይ ይዟል፡ በምድርም ይሁን ከምድር በታች፡ ወይም በየትኛውም ቦታ፡ መጽሐፉን ሊያይ የሚበቃ አንድ እንኳን አልተገኘም፡ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የታረደው በግ ግን፡ ያኔ መጀመሪያ ይህንን የተዋጀውን አካል ባሰበ ጊዜ፡ መጥቶ በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ከቀኝ እጁ ወሰደ፡ እሱ ራሱም፡ ተቀመጠ። አሜን፡ ይኸው። ቃሉ ይህ ነው። አያችሁ፡ እጅግ የሚያምር ነው።

94 አሁን፡ “እኔ ድል እንዳደረግሁ በአባቴ ዙፋን ላይ እንደተቀመጥሁ፡ ድል ለሚነሳ ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ እሰቀምጠዋለሁ።” በሌላ አባባል፡ “በሰውነቴ ማለት በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ እኖረዋለሁ። በመንፈስ ቅዱስ የዓለምን ነገር ሁሉ (በፈተናው) አሸንፌአለሁ፡ ተቆጣጥሬዋያለሁ!” (“በእርሱም የመለኮት

ሙላት በሰውነት ተገልጦ ይኖራል።”) “በሰማያትና በምድር ኃይል ሁሉ ለእኔ ተሰጥቶኛል፡” አለ። ኃይል ሁሉ! እንግዲያውስ እግዚአብሔር ሌላ አካል ከሆነ ኃይል አልባ ሆኗል። መጽሐፍ ቅዱስ፡ ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ፡ እንዲህ ብሏልና፡ “በሰማያይ እና በምድር፡ ሁሉ ላይ፡ ኃይል ሁሉ ለእኔ ተሰጥቶኛል።”

95 ኢየሱስም ከቅዱሳኑ ከእእላፋት ጊዜ እእላፋት ጋር ከሰማይ ይመጣል፡ ይላል መጽሐፍ ቅዱስ “ሰማያት ለግማሽ ሰዓት ያህል ባዶ ሆነ።” ታድያስ፡ ይህ ታላቅ አካል፡ ማለት እግዚአብሔር የት ገባ? ኧሃ-ሃህ። አያችሁ? በክርስቶስ ውስጥ ነው። በእርግጠኝነት! እኛም እንደ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ ድል ስንነሣ፡ የዳዊትን ምድራዊ ዙፋን ላይ ሲቀመጥ ከእርሱ ጋር እንቀመጣለን፡ እርሱ ከላይ እንደሆነው ሁሉ፡ (አሜን!) እኛም ደግሞ በምድር ሁሉ ላይ ከእርሱ ጋር በኃይል እና በስልጣን ለመግዛት እንቀመጣለን። “እነርሱም… የእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ፡ የእግዚአብሄር ልጅ እስኪገለጥ ድረስ እየተጠባበቀች፡ ምድር እያማጠች ትገኛለችና።”

96 ምክንያቱ፡ በመሰረቱ፡ ይህ ዓለም እግዚአብሔር እንዲገዛው የተፈጠረ አይደለም። ይህ ትክክል መሆኑን እናስተውል። የምድር አምላክ ማን ነው? ሰው ነው! ግዛቱ ነው። በምድር ላይ ያለው ሁሉ፡ ለሰው ይገዛል። በኃጢአት ወደቀ፡ በክርስቶስ የማዳን ኃይል እንደገና ተመለሰለት። እውነት ነው፡ ምክንያቱ ምድር የሰው ናት፡ ለእሱ ተሰጥቶት ነበር እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ገዥ ነበር። የእግዚአብሔርም ልጆች ዳግመኛ የሚገለጡበትን ጊዜ እየጠበቀ፡ ተፈጥሮ ሁሉ ምጥ ላይ ነው። ኧረ፡ ጉድ ነው፡ ኦህ፡ ማይ! የእግዚአብሔር ልጆች መገለጦች። አሁን፡ ያንን ለጊዜው ብናቆየው ይሻላል።

97 መልእክተኞቹ ግን፡ በቀኙ ሆነው፡ ወደሚልካቸውም ሁሉ ሄደው ለመናገር፡ ይጠባበቃሉ፡ በክርስቶስ የነበረው መንፈስ ቅዱስ… ኦህ! በክርስቶስ የነበረው መንፈስ! ሲሄድ፡ እንዲህ አለ፡ “ለጥቂት ጊዜ ዓለም፡” **ኮስሞስ**፡ የግሪክ ቃል ነው ትርጉሙም “የዓለም ሥርዓት” ማለት ነው፡ የምድር ሳይሆን፡ የዓለም፡ የዓለም ሥርዓት፡ “ከእንግዲህ አያየኝም፡” የኃይማኖት ተቋማት፡ ወይም ሌሎች፡ “ከእንግዲህ ወዲህ አያዩኝም፡ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡” ቤተ ክርስቲያን፡ አማኞችን፡ “ምክንያቱ እኔ፡” ትክክለኛ የግል ተውላጠ ስም፡ **እኔ፡** “እኔ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ በውስጣችሁ እኖራለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።” አያችሁት ወይ?

98 እንግዲህ በበዓለ ሃምሳ ቀን የመጣው ያ የክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ እነዚያን ነገሮች ካደረገ፡ **እዚህ** የተላከልን የክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ ነው፡ አሁንም **እዚህ** ድረስ ጸንቶ የሚኖረው የክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ ነው፡ **እስከዚህ** ድረስ የጸናው የክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ፡ እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ **እዚህ** ላይ አሁንም አለ። ጳውሎስን በመንፈስ ቅዱስ እና የሰራቸውን ሰራዎች የሞላው ያው መንፈስ ቅዱስ፡ **ይህንንም** (ኢራኒዎስን) በመንፈስ ቅዱስ በሙላት ይሞላዋል፡ ማርቲንን በመንፈስ ቅዱስ ይሞላዋል፡ ሌሎቹንም በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ይሞላቸዋል፡ እናንተንም እኔንም በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ይሞላናል፡ ይህም ከአንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ወደ ሌላኛው የሚተላለፍ የጴንጤቆስጤ በረከት ነው፡ አልፋ እና ኦሜጋ፡ መጨረሻውና መጀመሪያ፡ እና ሁሉም፡ የዳዊት ሥር እና ዘር፡ የንጋት ኮከብ፡ የሳሮን ጽጌሬዳ፡ የሸለቆው አበባ፡ ሌላው ሁሉ፡ አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ የነበረው፡

ያለውና፡ የሚመጣው፡ አልፋ፡ ኦሜጋ፡ ሁሉ፡ ሁሉም በሁሉ! ኦህ፡ ማይ! ዘምር ዘምር አለኝ፡

ኧረ፡ ማን ነው ትሉኛላችሁ፡ (አላቸው ኢየሱስ፡) ከየትስ እንደ መጣሁ ትላላችሁ፡
አባቴንስ ታውቁታላችሁን፡ ስሙስ ማን ይባላል?
እኔ አልፋና ኦሜጋ ነኝ፡ ይላል፡ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው፡
ፍጥረት በሙሉ **እኔ ነኝ**፡ ሰሙ ግን ኢየሱስ ይባላል።

በሚነድድ በእሳት ቊጥቋጦ ውስጥ ሙሴን የተናገርኩት **እኔ ነኝ**፡
የአብርሃም አምላክ **እኔ ነኝ**፡ ብሩህ የንጋት ኮከብ። (ትክክል ነው።)
የሳሮን ጽጌሬዳ **እኔ ነኝ**፡ ከየትስ መጣ ትሉኛላችሁ?
ፍጥረት በሙሉ **እኔ ነኝ**፡ ሰሙ ግን ኢየሱስ ነው።

99 በሰማይና በምድር ያሉ ሁሉ ቤተሰቦች በዚህ ስም (ዓለም አቀፋዊት፡ የተባረከች፡ በመንፈስ ቅዱስ-የተሞላች፡ የተረፈች፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሰየመች፡ በመንፈስ ቅዱስ የተነገረች፡ በመንፈስ ቅዱስ የተወለደች ቤተሰብ) ሰያሜ ትጠራለች፡ ትክክል ነው። እግዚአብሔር በሰማይና በምድር ላሉት ቤተሰብ ሁሉ ሰጣቸው። በውስጧ ያለው ሁሉ፡ ጉልበቱ ሁሉ፡ ለዚያ ስም ይንበረከካል። “እና ሰዎች የሚድኑበት ከሰማይ በታች የተሰጠ ሌላ ሰም የለም።” **ምናልባት** ሳይሆን፡ **በርግጥ**፡ መዳኛ የሚሆናቸው። አቤት፡ ደስ ሲል። በቃ ይመቻል። በጣም ጥሩ።

100 “በቀኝ እጁ።” አሁንስ ገብቷችኋል? እስከ አሁን ድረስ ኃይል፡ ምልክቶች፡ በሙሉ የሚደረጉባት፡ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ናት። አሁን ያለነው... ልትጠፋ በተቃረበችበት በጨለማው ዘመን ደርሳለች። አሁን 2ኛው ቁጥር እንወሰዳለን። ኦህ፡ ገና በጥቂቱ ከዚህ—ከ 1ኛው ዘንድ ትንሽ እንቆያለን፡

... **ሥራህን አውቃለሁ፡ ሕያው እንደ ሆንህ ስም** አለህ፡ **ሞተሃልም።**

101 ወደዚህ ወደሚቀጥለው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ዞር ስትሉ፡ “ስሜን ግን አልካድህም፡” እንዳለው ታገኛላችሁ። ቀጣይ ቤተ ክርስቲያን፡ “ስሜን አልካድህም።” **ይሄኛው** ቤተ ክርስቲያን ግን፡ “ስም **አለህ**።” ተከታተሉ! **ይህች** ቤተ ክርስቲያን ሰሙን ጠብቃለች፡ **ይህች** ቤተ ክርስቲያን ሰሙን ጠብቃለች፡ **ይህች** ቤተ ክርስቲያን ሰሙን ጠብቃለች፡ **ይህች** ቤተ ክርስቲያን በጨለማው ዘምን ሰላለፈች ሰለሷ ምንም አልተባለም፡ የመጀመሪያዎቹ ትንሽ አምልጠው፡ ሉተር አውጥቷቸው፡ **በዚህ** በኩል ወደ ሕይወት ሲወጡ፡ “ሕያው እንደመሆንህ ሰም አለ**ህ** ሞተህማል።” አሁን፡ የኢየሱስን ሰም መጠቀም ካቆሙ በኋላ ምን አይነት ሰም ተጠቀሙ? አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ። እና እንደዚህ ብሎ ነገር የለም። የሞተ ነው—የሞተ ቲኦሎጂ ነው።

102 እስቲ ንገሩኝ፡ አባት ሰም ነውን? ሰንት አባቶች አላችሁ? እጃችሁን ወደላይ አንሱ። ከእናንተ ሰሙ አባት? ልጆች? እና ሰዎች የሚባል ማን ነው? ያ’ማ—ያ ምንነቱ ነው። አይደለም... ሰሙ መንፈስ ቅዱስ አይደለም፡ ያ’ማ ምንነቱ ነው፡

**ራሱ** መንፈስ ቅዱስ ነውና። ስሙ... መንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም፡ መንፈስ ቅዱስ መዓርግ ነው፡ አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ።

103 ስለዚህ ይህ ነገር፡ ዘላለማዊ ልጅነት እንደሚሉት ተራ ነገር ነው። የዘላለም ልጅነት የሚባል ነገር የለም። የተወለደ ልጅ ከሆነ፡ በፍጹም ዘላለማዊ አይሆንም።

104 ባለፈው ምሽት እንዳልኩት፡ ዘላለማዊ ገሃነም፡ ብሎ ነገር የለም። የዘላለም ገሃነም ከየት አገኛችሁት? እንዲያ'ማ ከሆነ፡ ገሃነም ከመጀመሪያ ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን "ለዲያብሎስና ለመላእክቱ የተፈጠረ፡" እንደሆነ ይመሰክራል። የነበረ ነገር ከሆነ፡ ገሃነም አሁንም ይኖራል፡ እንዲያ ከሆነ ከመጀመሪያ የነበረ ሊሆን ግድ ነው። ታዲያ ያኔ... እሱ ገና **ኤል፡ ኤላህ፡ ኤሎሂም**—በነበረ ጊዜ ማን ይጠቀምበት ነበር፡ "በራሱ-የሚኖር፡" በአጠገቡ ማንም ሳይኖር ሳለ? ታዲያ ገሃነምም አብሮት ነበር ማለት ነዋ። አያችሁ? "ገሃነም የተፈጠረው ለዲያብሎስና ለመላእክቱ ነው። የክፉዎችም ሁሉ መጣያም ነው።" በትክክል ልክ ነው። ምናልባት ስለ ስራቸው ለአንድ መቶ ሚሊዮን ዓመታት ሊቀጡ ይችላሉ። ከዚያ በኋላ ግን ሁለተኛው ሞት የሚቀምሱበት ጊዜ ይኖራል። ያኔ ምናቸውም አይገኙም። መጀመሪያ ያለው ነገር መጨረሻ አለው። ስለዚህ እኛ የዘለአለም ህይወት ስንቀበል፡ የሞለኪውል ቅንጣት ከመኖሩ በፊት ከነበረው ከጠፈር ብርሃን በከፊል እየተቀበልን ነው። ኧሃ-ሃህ። ኢየሱስን ማየት እንድንችል የሚያበራልን የእግዚአብሔር ብርሃን ወደ ልባችን መጣ። መጽሐፍ ቅዱስ፡ "ሁሉንም ነገር አናይም፡ ኢየሱስን ግን እናያለን" ይላል።

105 አሁን፡ እንደተናገረው፡ "አውቃለሁ ብሏል... ወደ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የሚልኩትን ሰባቱን መንፈሶች ያለኝ እኔ ነኝ። ስራዎችህን እና ያለህን ሁሉ አውቃለሁ፡ ነገር ግን ህያው እንደመሆንህ ስም አለህ ሞተህማል።" አሁን፡ አስታውሱ፡ የማን ዘመን ነው? የማርቲን ሉተር፡ የሉተር ዘመን ነው። አሁን፡ ገና ከጅምሩ የተወገዙ ናቸው። መጀመር አያስፈልጋቸውም፡ ከጅምሩ የሞቱ ናቸው። መሞት አያስፈልጋቸውም፡ ከጅምሩ የሞቱ ናቸውና። አያችሁ፡ "ተነጥቀው የወጡ" ናቸው።

106 አሁን ይህን አስተውሉ። ቀጣዩን ጥቅስ እናንብብ፡

> ተከታተሉ! **የነቃህ ሁን፡ ሊሞቱ** ያሉትን፡ **የቀሩት ነገሮችን አጽና፡ ሥራህን በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትምና።**

107 አሁን፡ ሉተርን እየተናገረ ነው። ይህ ስለ ሉተር ዘመን—ስለ ተሐድሶው ዘመን እንደሆነ፡ ሁላችንም እንስማማበታለን። እሺ ምን አለው? "'ህያው' እንደመሆንህ የሐሰት ስም ይዘሃል፡ ሞተህማል።" ምን አደረጉ? በትክክል ወደ ኃይማኖት ተቋም መለሱት። እንግዲያውስ፡ "ማሰሮ ጀበናን 'ጥቁር' አትላትምና፡" "በካቶሊክ ላይ!" ጥሩምባ አትንፉ፡ አያችሁ፡ ተመሳሳዩን የእምነት መግለጫዎችን እና ሰሞችን በመጠቀም፡ ወደነሱ በትክክል ገብታችኋል። እና፡ እንግዲህ፡ ሉተር በካቶሊክ ዘንድ የነበሩትን እንደ ካተኪዝም የመሳሰሉ ነገሮችን አምጥቷል፡ እና እራሳቸውን ሰም አወጡ። አያችሁ፡ "'ህያው' እንደመሆንህ፡ ከሞተው ከሺህ አመታት ያወጣኸው ሰም አለህ፡ አሁንም ያንን ሰም ይዘሃል።" "**አንድ** ሰም አለህ፡" አስታውሱ?

108 ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ፡ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት፡ "ስሜን ጠብቀሃል፡" ተብለዋል። "ስሜን ጠብቀሃል።" **በዚህ** ዘመን ግን "ጠፋባቸው።" እና **እዚህ** ጋር ሲመጣ ግን "'ህያው' እንደመሆንህ ሌላ ስም አለህ፡ ሞተህማል፡" አለው።

109 እናንተ ሜቶዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ሉተራውያን፡ እና ጴንጤቆስጤዎች፡ ሆይ፡ ንስሃ ግቡ ስለ ሐጢአቶቻችሁ ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ተጠመቁ። አያችሁ? ካረጁ የሞቱ የእምነት መግለጫዎች እና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከሆኑ ነገሮች ውጡ ይህ ሁሉ ራሷን እና ልጆቿን ጨምሮ ሁሉም ተበልቶ ይጠፋል።

110 እንደዚህ ዓይነት ነገሮች "አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ፡" የሚሉት ነገር… እንዲሁም፡ "ቅድስተ ሰላሴ" ብሎ ነገር የለም። ሰላሴ? እስኪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ **ሥላሴ** የሚለውን ቃል ካለ፡ አንድ ሰው ፈልጎ እንዲያሳኝ እፈልጋለሁ፡ **ሥላሴ** የሚለውን ቃል እስኪ ፈልጉ። በዚያ ውስጥ አታገኙትም። እንደዚህ ያለ ነገር የለም።

111 አሁን፡ አሁን፡

… እና **ሊሞቱ ያሉትን፡…**

112 "ሉተር ነጥቆ አውጥቶሃልና፡ አሁንም የቀሩትን አጽንተህ ያዝ። ሊሞቱ ተቃርበዋልና፡ ያለህን አጽንተህ ያዝ። አንተም… እንደገና ወደዚያ ይጎትቱሃልና። ሊሞት ተቃርቧልና፡ ያለህን አጽንተህ ያዝ።"

113 አሁን፡

… **በእግዚአብሔር**ም ፊት ፍጹም ሆነህ **አላገኘሁህም።**

114 ደስ አይልም ወይ? ኦህ፡ ማይ! ይሄን ወደድኩት። "ፍጹም አይደለህም።" ለምን? የጸደቁ ብቻ ነበሩ፡ ሉተር ስለ ጽድቅ ብቻ ሰበከ፡ ከዛ ግን መቀደስ እና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ይቀራል። ስለዚህ የራሳቸው አይደሉም፡ በውስጣቸው ባለው በመንፈስ ቅዱስ ፍጹማን የሆኑ ናቸው እንጂ። በውስጣቸው ያለው ፍጹም መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ፡ ፍጹም የሆነው—ክርስትያኑ አይደለም። አያችሁ? ያ ነው… አስቀድሜ እንደተናገርኩት፡ "የተቀደሰ ተራራ ሳይሆን፡ በተራራው ላይ ያለው ቅዱስ እግዚአብሔር ነው። በቤተክርስቲያን እና በሰዎች ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡ ቅዱሳን ሰዎች ብሎ ነገር የለም።" **ቅዱስ** የሆነው ክፍል ያ ነው፡ እዩት።

115 "እና ስራህ ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትም። ወደ ፍጹምነት አትበቃም።" ምክንያቱም **እዚህ** ጋር ጽድቅ፡ ጽድቅ ላይ እንደነበሩ እናያለን። እና ይህም… አይደለም፡ ይቅርታ አርጉልኝ። **እዚህ** ጋር ጽድቅ በሉተር ሥር ነበረ፡ **እዚህ** ጋርም ቅድስና ሲሆን፡ መንፈስ ቅዱስም **እዚህ** ጋር ነበረ። አያችሁ? አሁን፡ በእነዚያ በሦስቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ውስጥ የሠሩት ሦስቱ ውህደቶች፡ ዳግም ልደትን ሙሉ የሚያደርጉ እነዚህ ናቸው። በእናት ማህፀን ውስጥ እንደ ትንሽ ህዋስ የተፀነሱ ብቻ ነበሩ። በትክክል፡ ለመወለድ መንፈስ ቅዱስ ይመጣል።

116 አንድ ነገር ልጠይቃችሁ። በተፈጥሮ ልጅ ሲወለድ፡ ከሁሉ ቀድሞ የሚመጣ ነገር ምንድነው? ውሃ። ቀጥሎ የሚመጣስ? ደም። ልክ ነው? ቀጣይስ? መንፈስ ነው። በትክክል።

117 ኢየሱስ ሲሞት ከሥጋው ምን ወጣ? ጎኑን በወጉ ጊዜ፡ ውሃና ደም ወጣ፡ "መንፈሴን ለእጅህ አደራ እሰጣለሁ።" ውሃ፡ ደም፡ መንፈስ።

118 "ስለዚህ በእምነት ከጸደቅን፡" ሮሜ 5:1 ላይ፡ "ከእግዚአብሔር ጋር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም አለን፡" መጽደቅ። ቅድስና፡ ዕብራውያን 13:12 እና 13፣ "ኢየሱስ ሕዝቡን በደሙ እንዲቀድስ ከበሩ ውጭ መከራን ተቀበለ።" ሉቃስ 24:49፡ "እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ። መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ፡ **ያኔ** በኢየሩሳሌም፡ በይሁዳ፡ በሰማርያ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ… "

119 ቢሾፕ ከሆናችሁ በኋላ አይደለም፡ ዲያቆን ከሆናችሁ በኋላ አይደለም፡ ፓስተር ከሆናችሁ በኋላ አይደለም፡ ጳጳስ ከሆናችሁ በኋላ አይደለም፡ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ፡ ያኔ ምስክር ትሆኑኛላችሁ።" ዲያቆን ብቻ ከሆንክ… ስለ ቤተ ክርስቲያንህ፡ እና ስለ እምነትህ ብቻ ትመሰክራለህ፡ ወይም ፓስተር ብቻ ከሆናችሁ፡ ጳጳስ ብቻ ከሆናችሁ፡ ወይም ሌላ… የኃይማኖት መግለጫ መዝገብ ያዥ ትሆናላችሁ! መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ ግን፡ ስለ እርሱ ትመሰክራላችሁ! ሕይወቱ በውስጣችሁ ስለሚሆን፡ እርሱ የሠራቸውን ሥራዎች፡ እናንተም ታደርጋላችሁ። አቤት፡ አቤት! ማይ፡ ማይ! ልክ እንደዛ። አዎን፡ ወዳጄ። አቤት፡ እዚያ ካላችሁ ከሁላችሁ ይልቅ፡ እኔ እዚህ ሆኜ፡ የገባኝ ነገር እንዳለ፡ እምናለሁ። በዚህ ነገር ደስ ይለኛል።

120 "ሊሞቱ ያላቸው ነገሮች፡ አጥብቀህ ያዝ።" አሁን በ3ኛው ቁጥር ላይ፡ እዚህ እንደተናገረው፡

> **እንግዲህ እንዴት** እንደ **ተቀበልህና እንደ ሰማህ አስብ፡** (ወደድኩት።) **እናም አጥብቀህ ያዝ፡ ንስሐም ግባ። እንግዲህ** ባት**ነቃ፡ እንደ ሌባ እመጣ**ብሃለሁ፡ በ**ማናቸውም ሰዓት** እንድ**መጣብህ… ከቶ** አ**ታውቅም።**

121 "ጽድቅህን ጠበቅ አድርግ፡ አጥብቀህ ያዝ።" ሰዎች ይህን እንዲወስዱብህ አትፍቀድላቸው። "ያም ደግሞ አንተ የተቀበልከው፡ እንዲሁም የሰማኸው።" እኛ የምናነበው መጽሐፍ ቅዱስ ያነባሉና፡ አያችሁ። ይሁን እንጂ ለእነርሱ ስላልተገለጠላቸው፡ በሙላት አይወስዱትም። ለዘመናቸው የተሰጠ አይደለምና። በትንሣኤ ጊዜ የሚመጡበት ምክንያትም ይህ ነው። መራመድ በነበረባቸው ብርሃን ውስጥ ተጉዘዋል፡ ስለዚህ ይመጣሉ።

122 አሁን፡ ጥምቀትን የሚሰብኩ ብዙ የጴንጤቆስጤ ሰዎች፡ እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡ "ሉተራኖች፡ እና የመሳሰሉት፡ አይመጡም።" ኦህ፡ አዎን። እዚያ ማዶ ላይ ያለው የዶር. ሄግሪ ትንሽ ታሪክ ታውቃላችሁ። "እኛ ምንድን ነን፡" ብሎ በጠየቀኝ ጊዜ… ያልኩትን? ነገርኩት… በቤታኒ፡ ሚኒያፖሊስ ውስጥ፡ ያንን ታላቅ የሉተራን ትምህርት ቤት፡ መስራታቸውን ታውቃላችሁ። እርሱም አለኝ፡ "እሺ፡ እኛ ሉተራኖች ያለን ነገር ምንድነው? "

እኔም "እሺ፡ እነግርሃለሁ። ክርስቶስ እንደተቀበላችሁ እምናለሁ፡" አልኩት።

እርሱም፡ “እሺ፡ እኛ—እኛ መንፈስ ቅዱስን እንፈልጋለን።” “ያለን ይመስልሃልን፡” አለኝ?

እኔም አልኩት፡ “በቅጡ ባይሆንም አላችሁ።” “እምነታችሁ ስለሉ ነው፡” አልኩት።

እሱም “እንዴ፡ ምን ማለትህ ነው፡” አለኝ?

123 እንግዲህ፡ ለተማሪዎቻቸው በሺዎች የሚቆጠሩ ሄክታር መሬት አላቸው... ወጪዎቻቸውን—መሸፈን ካልቻሉ፡ ሰርተው በቆሎ እንዲያመርቱ ያስደርጓቸዋል። እኔም አልኩት፡ “እንግዲህ... ” በዚያም ትልልቅ—ጠረጴዛዎች ተደርድረዋል። በዚያ ትልቅ ሴሚናሪ ውስጥ አንዱን የእራት ገበታ ጠረጴዛ ለእኔ ሰጥተውኛል። እንግዲህ አሁን፡ ሰዎቹ መልካሞች ናቸው፡ ዶር. ሄግሪ **በዚህ** በኩል ቁጭ ብሏል፡ ወንድም ጃክ ሞር **በዚያ** በኩል፡ እኔ ወደሱ ጠጋ በማለት ቁጭ ብዬ ነበር ምክንያቱም እኔ የማላውቀውን ትልልቅ ቃላትን መናገር ከጀመረ፡ ጃክን በእግሬ ልመታው እና የተናገረውን ልጠይቀው ፈልጌ ነው፡ እያችሁ። ስለዚህ፡ እንዲህ አልኩት...

124 አጠገቤ ተቀመጠና፡ እንዲህ አለ፡ “እንግዲህ፡ እኛ የምናደርገው ሁሉ የሆነ ነገር ፍለጋ ነው።” “ረሃባችን እግዚአብሔርን ነው፡” አለኝ። እንዲህም አለ፡ “ስለ ጴንጤቆስጤ፡ **ሰጦታዎችን** በተመለከተ አንድ መጽሐፍ አነብበናል።” እንዲህም አለ፡ “ብዙ ሆነን... ወንድሞች ተሰብሰበን ወደ ካሊፎርኒያ ሄድን፡ ያንን መጽሐፍ የጻፈውን ሰው አገኘነው።” (ሰውዬው እኔም አውቀዋለሁ።) እንዲህ አለ፡ “‘ጥቂት ሰጦታዎችን በተግባር ለማየት ተመኘን።’ እርሱም አላቸው፡ ‘እንዲሁ ጻፍኩት እንጂ፡’ ‘እኔ ለራሴ አንዳቸውም የሉኝም፡’ አላቸው።” እና እንዲህ አለ... እንዲህም አለ፡ “በዚያም ስንመጣ ይህን ባየን ጊዜ፡ እጅግ ተራብነው። እግዚአብሔርን ፈለግን።”

125 እኔም አልኩት፡ “እንግዲህ፡ አንድ ጊዜ አንድ ሰው ወጣና።” እንደው፡ በገዛ ማሳው ነው፡ እያችሁ። “ይህ ሰው ወጥቶ ሰፊ የእርሻ መሬት አስተካከለ። ሥራሰሮቹን በሙሉ ቆፈረ፡ ሌላ ሌላ ነገሮቹም ሁሉ አሰወገደ፡ ከዚያም በቆሎን ዘራበት። በየማለዳው ወደ በሩ ሄዶ በቆሎ ማውጣቱን አለማውጣቱን ያያል። እና በመጀመሪያ የሆነውን ታውቃላችሁ፡ አንድ ቀን ጠዋት፡ ሁለት ቅጠሎች ብቅ ብለው ታዩ።” (በቆሎ አምራች የሆናችሁ ሁላችሁ... እነ ጆርጅ ራይት እና ሌሎቻችሁ፡ እነ ሮይ ስሎውት እና ሌሎቻችሁ? እነዚያን ብቅ ያሉትን ቅጠሎች፡ ታውቃላችሁ አይደል።) “‘ኦህ፡’ ‘ስለ በቆሎ እርሻዬ እግዚአብሔር ይመስገን’ አለ።”

እኔም አልኩት፡ “ይህ ሰው የበቆሎ ማሳ አለውን? ”

እሱም “መቼም፡ በተወሰነ መልኩ፡” አለኝ።

126 እኔም “በቅጡ ባይሆንም፡ አዎን፡” አልኩት። “በመጀመሪያው ተሐድሶ ላይ ያበቀላችሁት የመጀመሪያ ቅጠሎች፡ እናንተ ሉተራኖች ነበራችሁ፡ አየህ፡” አልኩት። “እንግዲህ፡” አልኩት፡ “ያን ጊዜም በቆሎው አደገ።” ስለ “ድንዛዜው” አልነገርኩትም፡ እያችሁ፡ ስለ በቆሎው፡ እርሱም ማደጉን እንዲያስብ ብቻ አደረግኩት።

127 ስለዚህ አልኩት፡ “በቆሎውም አደገ፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በላዩ ላይ አበባ አበቀለ። ያቺ አበባም ወደ ቅጠሏ ዝቅ ብላ አየችና እንዲህ አለቻት፡ ‘ሃ-ሃ-ሃ-ሃ-ሃ፡ እናንተ እርባና ቢስ ሉተራኖች፡ ባዶ ናችሁ።’ አያችሁ? ‘ፍሬአማዋ... ታላቋ የሚሽነሪ ዘመን፡ እኔ—ነኝ፡’ አለች። ንፋሱ ነፈሰ፡ እና ትንንሾቹ አበቦች እንዲህ ጠውልገው ወደቁ፡ ያም የዌስሊ፡ ቅድስና ነው።” አያችሁ? እስካሁን ካየናቸው ትልቁ የሚስዮናውያን ዘመን ያ ዘመን ነው፡ የዌስሊያውያን ቤተክርስቲያን ዘመን፡ ከዌስሊ ዘመንም ይሁን፡ ከዚህ ዘመን ይልቅ የሚበልጥ ነበር። የዌስሊያውያን ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ የሚስዮናውያን ዘመን ነበር፡ ስለዚህ ተዘርግቷል። ምን አደረጋት፡ ራሱ—ዘረጋት።

128 አያችሁ፡ ተፈጥሮ እንኳ ሳይቀር፡ ስለነዚህ ስለ ሶስቱ ይመሰክራል። ተፈጥሮ እራሷ፡ እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠረው እንደዛ ይሆን ዘንድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ እያስፈልጋችሁም፡ ተፈጥሮን በማየት ብቻ የት እንዳላችሁ ማየት ትችላላልችሁ። አያችሁ?

129 ከዚያ በኋላ... ከጥቂት ጊዜ በኋላ በዚያው ተዘረረች። ከዚያስ ምን ወጣ? የበቆሎ ሸፋን ወጣች፡ በውስጧም እህል ነበረባት፡ ይህም የጴንጤቆስጤ ቡድን ነበር። አሁን፡ እነዚህ የጴንጤቆስጤ ቡድን **እዚህ** ታች ካሉት ቡድን አንድ አይነት ነበሩ። **ከዚህኛው** ሁለት የበቆሎ ቅጠሎች ተገኙ፡ ሉተር፡ **እዚህ** ላይ አበባ ተገኘ፡ ዌስሊ፡ እና **እዚህ** ላይ ደግሞ የበቆሎ እህል ተገኘ (ምን? ) ልክ **እዚያ** እንደነበረው አይነት ወጣ። ተመሳሳይ ነው!

130 እሺ እንግዲህ፡ እዚህ ጋር የነበረው ምን ነበረ? “እሺ፡ እንግዲህ፡” ትላላችሁ፡ ጴንጤቆስጤዎች እንዲህ ይላሉ፡ “እናንተ ሜቶዲስት ወይም እናንተ ሉተራውያን ከእናንተ ጋር ምን አለን።” ግን'ኮ፡ አበባው እንዲወጣ ያደረገው፡ በሁለቱ ትንንሽ ቅጠሎች ውስጥ የነበረው ህይወት ራሱ ነበር። በአበባው ውስጥ የነበረው ህይወትም በቆሎውን እንዲያፈራ አደረገ። ስለዚህ፡ ተመልከቱት፡ ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበረ። በቅጡ ባይሆንም፡ መንፈስ ቅዱስ ነበራቸው፡ ዌስሊም፡ በቅድስና ስር እንዲሁ ነበረው፡ ዛሬ ግን በልሳኖች መናገርን እና የመጀመሪያውን ነገሮች **ወደዚህ** መቃናት ሆኗል። ያው መንፈስ ቅዱስ፡ አያችሁ፡ ዋናዎቹ ላይ። አሜን። አዎን።

131 በጣም ጥሩ፡ “የሰማኸው ነገር እንዳይጠፋ፡አጥብቀህ ያዝ።” አሁን ይመስለኛል፡ 4ኛው ቁጥር፡

> **ነገር ግን ልብሳቸውን ያላረከሱ በሰርዴስ ጥቂት ሰዎች ከአንተ ጋር** አሉ፡ **የተገባቸውም ስለ ሆኑ፡ ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ ጋር ይሄዳሉ።**

132 “አሁን፡ ከዚህ የኃይማኖት ተቋም ለመስራት አልፈልግም፡ ያንን የማድረግ ፍላጎት የለንም።” አይ፡ የተሳሳተ... ጥቅስ ያነበብኩ—ይመስለኛል፡ አይደልም'ዴ? ወይስ ልክ ነኝ? አዎን፡ አዎን፡ ልክ ነኝ። አዎን። በጣም ጥሩ። አዎን፡ “ልብሳቸውን ያላረከሱ፡ በሰርዴስ።” እራሳቸውን በንጽሕና እና በጥራት ጠብቀው፡ ለዚያ ነገር ያልሰገዱ ጥቂቶች በመካከላቸው ነበሩ፡ እነዚህም ከጥንት ከጴንጤቆስጤ ጀምሮ እየተወራረሱ የመጡ፡ በመንፈስ-የተሞሉ ናቸው። ከዚያም ብዙዎቹ፡ የሉተር ዘመን ተቋም መሆን ሲጀምር፡ ምን አደረጉ? መጽሐፍ ቅዱስ እንደተናገረው “እንደ እናታቸው በመሆን።” ወደ ኋላቸው

መመለስ ጀመሩ። ወድያውኑ፡ ተቋም ወደ መሆን ተመለሱ። ጥቂቶቹ ግን እምቢ በማለት፡ ለእግዚአብሔር ታምነው ጸኑ። እንዲህ ይላል—ይናገራል፡ እንዲህ በማለት፡ “አዎን፡ ይሁን እንጂ፡ የተገባቸው ስለ ሆኑ፡ ነጭ ልብስ ለብሰው በፊቴ የሚመላለሱ፡ ጥቂት ሰዎች በአንተ ዘንድ አሉ። ተቋምን አታድርጉ። እንደው፡ የኒቆላውያን ዶክትሪን አትቀበሉ። በእግዚአብሔር ዘንድ አርነታችሁን ጠብቁ እንጂ፡ እንደገና የራሳችሁ የኃይማኖት ተቋም አትሰሩ። በነገራችሁ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ይምራችሁ። የቀሩ ጥቂት አሉ።”

133 አሁን 5ኛው ቁጥር፡ ይመስለኛል፡

**ጆሮ ያለው፡ ይሰማ...**

134 እሰኪ እንየው። አይደለም።

**ድል የነሣው፡ እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጐናጸፋል፡ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ... አልደመሰስም፡ በአባቴና** በ**መላእክቱም ፊት፡ ለስሙ እመሰክርለታለሁ።**

135 ይህም፡ “ጥቂት ሰዎች።” በጣም ጥቂቶች፡ ትንሽ ቅሪቶች፡ በካቶሊክ አስተምህሮ... ገና... ያልተወሰዱ በሌላው መንገድ ያልተጓዙ አሉ። በጣም ጥሩ።

136 አሁን ይህን ሁሉ ያመጣነው ስለ ተሐድሶ ለመናገር ነው። ደስ የሚለኝ ነገር... ወደዚህ እንድገባ የሉተርን ታሪክ አስቀርቼዋለሁ። አሁን የሚቀጥለው ጥቅስ እንዲህ ይላል፡

**መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን፡ ጆሮ** ያለው **ይሰማ።**

137 እግዚአብሔር፡ ከኒቆላውያን እንዲርቁ ሊያስጠነቅቃቸው እየሞከረ ነው፡ “ከእንደዚህ አይነት ነገር ራቁ! ልብሳችሁን ከየትኛውም የአለም እድፈት ጠብቁ!” በእርሱ ነፃ ሆነው ከጠበቁት፡ እርሱም ይመራቸዋል መንገድ ያሳያቸዋል። አሁን፡ የጅማሬው መነሻ ይህ ነው።

138 አሁን፡ **ተሐድሶ** ስል “ያመለጡ፡” በሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ያመለጡት ማለት ነው። ምን ማለቴ እንደሆነ ገብቷችኋል? አሁንም ከዚያ አስቃቂ ነገር ያመለጡ። እንግዲህ... አሁን፡ ነገ ማታ በድጋሚ አንስተን ወደዚህ በማምጣት... ወደ ጴንጤቆስጤ ዘመን አምጥተን፡ በትክክል ያ እንደሆነ እናሳያችኋለን። ስለዚህ፡ እዚህ የምንነጋገርባቸው ጥቂት ነገሮች፡ አንዳንዶቹ እነዚህ ናቸው፡ ያንን “እንዴት እንዳመለጡ? ” እንግዲህ፡ ያንን በሚቀጥለው ዘመን ላይ፡ እናነሳዋለን። አያችሁ፡ አንድ ላይ እንደሚሄዱ ለማድረግ እናነሳዋለን። እንዲህ ካላደረጋችሁ ግን፡ በቀጣዩ ዘመን ላይ በመስካት... ህዝቡን—የተሳሳተ ነገር ት—ት—ት—ትሰጡታላችሁ፡ አያችሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ባስቀመጣቸው መንገድ ማስተላለፍ ይገባችኋል፡ እሺ። በጣም ጥሩ።

139 አሁን፡ እየተናገረ ያለው ሰላመለጡቱ ነው። **እዚህ** ጋር የሚታዩት፡ እነዚያ እናሳ ቡድን ስለ ጽድቅ የሚኖሩ እነሱ ናቸው። አሁን ተመልከቱ! ብርሃን አይተው፡ ሉተር ያበራውን ብርሃን ስላዩ፡ ወጡ... ከሉተር ሞት በኋላ ግን፡ እንግዲህ ሉተር ራሱ አይደለም፡ ከሱ በኋላ የነበሩ ሰብሰቦች እንጂ፡ ሉተር ምንም አይነት ተቋም አላደራጀም። ከዌስሊ በኋላ የነበሩ ሰብሰቦች እንጂ፡ እሱም ምንም አይነት ተቋም አላደራጀም። ከእነሱ በኋላ ያለው ቡድን ነበር እንጂ፡ የጴንጤቆስጤ

መስራቾች ፈጽመው ተቋም አላደራጁም። ያንን የሚያደርጉት ሌሎቹ ናቸው፡ አያችሁ፡ ሁለተኛው ትውልድ ነው። እውነተኛው የብርሃን መልአከ መቼም ቢሆን ድርጅት አይፈጥርም! በዚህ በጴንጤቆስጤ ዘመን—በዚያ ድርጅት መጨረሻ ላይ የገጠማት ነገር ምን እንደነበረ፡ አያችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ሲገልጽልን፡ ታዩታላችሁ።

140 አሁን፡ እንዲህ አለ፡ "ትንሽ ብርሃን፡ በሰሱ ትንሽ ቀርታልሃለች፡ ሊሞት ተቃርቧል፡ እየተንገዳገደ ነው፡ መጽደቅ ብቻ ነው፡ በማንኛውም ሁኔታ ሊያንሸራትቷችሁ ይችላሉ። የተሳሳተ ስም ተቀብለሃልና፡ አሁንም ህይወት የለህም። ቢሆንም ግን… ቢያንስ—ቢያንስ ተነጥቀህ ወጥተሃል። አያችሁ፡ ከሮማ ቤተክርስትያን… አምልጠሃል—ሸሽተሃል። ዶግማውን በሙሉ አምልጠሃል፡ ቢያንስ ይህን ያህል ርቀህ ወጥተሃል።" አሁን፡ ያንኑ መጽሐፍ ቅዱስ እያነበብከው ነው። እንግዲህ፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚያስተምረው ያው መጽሐፍ ቅዱስ… በእነርሱ ላይ በነበረ ነገር ምክንያት እነርሱን አልኮነናቸውም። "ያ ግን… እኔ እስክመጣ ድረስ ያለህን አጥብቀህ ያዝ፡ አየህ፡ ብደንብ አጽናቸው፡" ብቻ አላቸው።

141 እንግዲህ፡ ይህ የቤተክርስትያን ዘመን የሚጀምረው፡ ሮማዊት፡ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ነገሮችን በሙላት በተቆጣጠረችበት በ1520 ነበር። ይህም (ማስታወሻ እየያዛችሁ ከሆናችሁ) እስከ ጥቅምት ሰላሳ-አንድ ቆየ። እስከ ጥቅምት ሰላሣ-አንድ፡ 1570 **ዓ.ም.**፡ ማርቲን ሉተር በጀርመን አገር፡ በዊተንበርግ በነበረው ቤተክርስቲያን በር ላይ ዘጠና-አምስት ቴሲሶችን በለጠፈ ጊዜ ነው፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ተሐድሶ በይፋ ተለኮሰ። ቀኖቹን እየያዛችሁ ናችሁ? እርግጠኞች እንድትሆኑ ደግሜ ልንገራችሁ። ማርቲን ሉተር በዊተንበርግ በነበረው ቤተክርስቲያን በር ላይ ዘጠና-አምስት ቴሲሶችን በለጠፈ ጊዜ፡በጥቅምት ሰላሣ-አንድ፡ 1570 **ዓ.ም.** ነበረ፡ ዊ-ተ-ን-በ-ር-ግ፡ ዊተንበርግ፡ ጀርመን። ተሃድሶው ከታወጀበት ቀን ጀምሮ፡ እሳቱ እየተቀጣጠለ መብረር ጀመረ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በዚያ በቆመችበት፡ በእጆቹ እንዲህ እንደያዘ፡ እንዲህ አለ፡ "የክርስቶስ አካል የምትሉት ይህ ነውን? ተራ ዋፈር እና ወይን ብቻ ነው!" እና ወደ መሬት ወርውሮ "ጧ!" አደረገው። ይህ እውነት ነው።

142 እሱ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተቃወመ፡ እና… ትንሿ-ትንታግ… መውጣት ጀመረች። በጣም ጥሩ፡ ያም… እንዲሁ ነበር። ያ ግን በይበልጥ—ስለ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ይልቅ፡ ለክርስቲያናዊ ሰልጣን ከነበረው ፖለቲካዊ ሹክቻ የሚደረግ ትግል ነበር። የታገሉት ከቤተክርስቲያን ወጥተው ሌላ ቤተ ክርስቲያን እንዲመሰርቱ ለፖለቲካዊ መብት ብቻ ነው። ክደውታልና፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ መንፈስ ቅዱስን እና ኃይልን ለማምጣት ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ወጥተው፡ ምንም ተሐድሶ አላደረጉም። አሃ? የፖለቲካ ሰልፍ ነበር። እርግጠኛ ሰፍራው ያ ነበር፡ "ህያው እንደመሆንህ ስም አለህ፡ ሞተህማል።" በሌላ አነጋገር፡ የፕሮቴስታንት የኃይማኖት ተቋም ብቻ አወጣ፡ ያ ብቻ ነው። ሴት ልጇን ከቤተ ክርስቲያኒቱ አወጣት ብቻ ነው። ከ… ከጋለሞታ ሴት ሴተኛ አዳሪ አወጣ ነው። የሆነውም ያ ነው። ጎቶልያን ከኤልዛቤል አወጣት።

143 አሁን፡ ስለ ተሐድሶ ያነበበ ማንም ሰው ያ እንደሆነ ያውቃል፡ ምክንያቱም በቀላሉ… ጥቂት የድሮ ቅርሶች እና ሥርዓቶች… እና በዓላት፡ እንዲሁ—ዝም

ብሎ አፈረሰ እንጂ፡ **እዚህ** ጋር እንደነበረው አይነት፡ መንፈስ ቅዱስን ወደ ቤተ ክርስቲያን መልሶ እስከ ማምጣት ድረስ አላደረሰም። አላደረሰም፡ ወዳጄ። ከመንፈሳዊ ተጋድሎ ይልቅ የፖለቲካ ሹክቻ ነበር። ከመንፈስ ቅዱስ ይልቅ ፖለቲካ ነበር። ገና ወደ ቤተ ክርስቲያን አልደረሰም ነበር። ወንድሜ ሆይ፡ አልተመለሰም፡ **ወደዚህች** መጣ እንጂ **ወደዚያ** አይደለም።

144 ስለዚህ፡ ታክላቅ የፖለቲካ ሰልፍ ነበር፡ ያ ግን ለመንፈስ ቅዱስ—ወይም ለቅዱስ ቃል አልነበረም። አንዳንድ የቀደሙ የመስቀል ቅርሶችን ያስወገደ የፖለቲካ ሰልፍ ነበር፡ እንዲሁም **"ሰላም ለኪ ማርያም፡"** የመሳሰሉ ነገሮችን አስወገደ። አሁንም ድረስ ግን ካቴኪዝም ይዞ ወጣ። አሁንም ያ ነገር ይዞ ወጣ… ማን ነበር የምትሉት? ምንድነው በፋሲካ ማለዳ ላይ ሲገለገሉ እዚያ ላይ የሚያደርጉት የቅድስና አገልግሎት ታውቃላችሁ፡ ፓስተሩም "መልካም ገና" ይላቸዋል። "ከእንግዲህ እስከ ገና ድረስ አታዩአቸውም፡" ይላቸዋል፡ እንደምታውቁት። ያ… ኦህ፡ ማለት የፈለግኩት፡ ማረጋገጫ—የማረጋገጫ አገልግሎት ነው። ቁጭ ያደርጓቸዋል ያረጋግጥላቸዋል፡ የመጀመሪያውን ቁርባን ሰጥተው ማረጋገጫ ያደርጉባቸዋል። ማረጋገጫ የሚባል ነገር የለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው ብቸኛው ማረጋገጫ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ—ከተባለ፡ እግዚአብሔር በሚከተለው ምልክትና ድንቅ ቃሉን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው። ማረጋገጫው፡ የሉተራን ቤተክርስትያን አባላት ስለመሆናችሁ ማረጋገጥ ሳይሆን፡ እግዚአብሔር ቃሉን በእናንተ ውስጥ የሚያረጋግጥ ስለመሆኑ ነው። "በሚከተለው ምልክት ቃሉን እያረጋገጠላቸው፡" "ጌታም ከእነሱ ጋር… አብሮ ይሰራ ነበር፡" ማርቆስ 16። የጴንጤቆስጤ ቤተክርስትያን ማረጋገጫ ያ ነው። እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ውስጥ፡ እንደ ተአምር-አድራጊ አምላክ ህያው መሆኑን የሚያረጋግጥበት-… ማረጋገጫው፡ ልሳኖች በመናገር፡ ልሳኖችን በመተርጎም፡ እና በመጀመሪያ ያደረጉትን ነገሮች አሁንም በማድረግ ነው።

145 አደከምኳችሁ እንዴ? [ጉባኤው "አላደከምከንም፡" አለ፡—አርታዒ።] እሺ እንግዲህ። አሁን፡ አስተውሉ፡ አዲስ የቤተክርስትያን ዘመን ብቻ አመጡ እንጂ፡ የመንፈስ ቅዱስ ሪቫይቫል እንደገና አላመጡም። የፕሮቴስታንት የስልጣን ተዋረድ ለማድረግ፡ በንጥቂያ-የወጡትን፡ አምልጠው የወጡትን አመጡ። ያደረጉት ያ ብቻ ነው። አያችሁ፡ ከመጋገሪያው ውስጥ ወዲያውኑ ወደ እሳቱ ዘለለው ገቡ። እ—እውነታው ይህ ነው። በትክክል።

146 ኤልዛቤል ሴት ልጅ ወለደች። እና አሁን ይህን ለማለት ብቻ—ብልህ ለመሆን የምለው አይምሰላችሁ፡ ይህን የምለው መጽሐፍ ቅዱስ ስለተናገረ ነው! መጽሐፍ ቅዱስ፡ በራዕይ 17 ላይ፡ "የጋለሞታዎች እናት ነች፡" ይላታል። እዚህ ላይ ኢየሱስ "ልክ ኤልዛቤል እንደነበረች፡ እንዲሁ እሷም ትሆናለች፡" ይላል። ያልረከሰች አገር የሚያረክሱ—ሴቶች ልጆች ወለደች። እንግዲህ፡ ፕሮቴስታንትም በእውነተኛው የእግዚአብሔር መንፈስ ላይ ያደረገው ያ ነው፡ ነገሩን አራክሶ ወደ ሌላ ተቋም ውስጥ መለሰው። ያም፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ በእሁድ ጠዋት፡ ያን ነገር ላሳያችሁ እፈልጋለሁ ለ—ለ—ለአውሬው ምስል እንዳደረጉለት፡ አውሬውም ሮም እንደነበረ። እና **እንደዚህ** አይነቱ ምስል አደረጉ። ያ ምን ነበር? ድርጅት! አቤት፡ ይህ ነገር በሰዎች ልብ ውስጥ እንደሚሰርጽ ተስፋ አደርጋለሁ።

147 እና ለምን በሕይወቴ ሁሉ ድርጅቶችን እንደተዋጋሁ ትገረማላችሁ፡ ለእኔ ለራሴም አይገባኝም ነበር። ነገር ግን እኔ ልቆጣጠረው የማልችል፡ በውስጤ የሚጮህ አንዳች **ነገር** ስለነበረ ነው። ይገርመኛል፡ በሴቶች ጉዳይ ላይ ሁሌ መቸገሬ ለምን እንደነበረ፡ ሁሌ ይገርመኛል? አያችሁ? ህይወቴ በሙሉ ነው። እውነተኛ-... እውነተኞቹ ሴቶች ላይ... ማለቴ አይደለም፡ እናንተም ታውቋቸዋላችሁ፡ ማለቴ ነገሮቻቸው እና የሞራል ወኔ የተበጠሰባቸው፡ **ተብዬዎቹን** ማለቴ ነው። ታውቋቸዋላችሁ። በእኔ ውስጥ ያለው **የሆነ ነገር**... ይህ አይነት ነው።

148 ያኔ ድሮ፡ ገና ታዳጊ፡ ትንሽ ልጅ ሳለሁ፡ እነዚያን አይነት ሴቶች፡ መንገድ ላይ ሲመጡ አያቸው ነበር፡ እና... ባሎቻቸው ስራ ሊሰሩ እንደወጡ ይታወቃል፡ እነርሱ ግን ከሌሎች ወጠምሾች ጋር፡ ሰክረው፡ ሰካራቸው እንዲለቃቸው፡ እና ለባሎቻቸው ምግብ ማብሰል እንዲችሉ፡ መንገድ ዳር ላይ ከላይ ወደታች፡ መንገድ ላይ እንዲህ ያመላልሷቸው ነበር። ንጹህ ጥይት በሰቷቸው ያልፍ ዘንድ ብቁ አይደሉም እል ነበር። እውነት ነው። እንደዚህ አይነት ተግባር ሲፈጽሙ፡ ከእንስሳ በታች ናቸው እላለሁ። እና ያኔ... አስራ ሰባት፡ እና አስራ ሰምንት አመት በነበርኩ ጊዜ፡ ሴት በመንገድ ላይ—ሰትመጣ ካየሁ፡ ወደ መንገዱ ማዶ ተሻግሬ፡ "ይህች ክፉ እፉኝት፡" ደግሞ መጣች እል ነበር። አያችሁ? እና በጣም ነበር የምጠላቸው፡ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በልቤ በተቀበልኩ ጊዜ ግን፡ በዚያም እግዚአብሔር አንዳንድ ጌጣጌጦች እንዳሉት እንድረዳ አደረገኝ፡ አንዳንድ እውነተኛ እመቤቶች አሉት። ሁሉም እንደዚያ ራሳቸውን አያረክሱም፡ ለዚህም እግዚአብሔር ይመስገን።

149 አፍሪካ ውስጥ በነበርኩ ጊዜ፡ ስዊዘርላንድ ውስጥ በነበርኩ ጊዜ፡ እና ሮም በነበርኩ ጊዜ፡ ይህን ጥያቄ አብዝቼ ጠይቄአለሁ፡ "እንዴ፡ ሰማ እንጂ፡ ወንድም ብራንሃም፡ በአሜሪካ ውስጥ ምንም አይነት ጨዋ ሴት የላችሁምን? ዘፈን በተለቀቀ ቁጥር፡ ስለሴቶቻችሁ የቆሸሸ ነገር ያቀነቅናል።"

150 እኔም እላቸዋለሁ፡ "እነሱ አሜሪካኖች ናቸው። በዚያ አገር ውስጥ ግን ህያው የሆነች ሌላ መንግስት አለች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ናት፡ ሴቶቿም ድንቅ ወይዘራዝርት ናቸው።" አዎን ናቸው!

151 መጽሐፍ ቅዱስ፡ በነቢያት ዘንድ—ይመስለኛል... ኢሳያስ 5ኛ ምዕራፍ ላይ፡ ሲናገር፡ እርግጠኛ አይደለሁም፡ 5 ኛ ወይም 6 ኛ ምዕራፍ ውስጥ ይሆናል፡ "የጽዮን ልጅ በዚያ ቀን ከሁሉ ታመልጣለችና፡ ብጽዕት ናት፡" በማለት ይናገራል። በመንገድ ላይ እንዴት እንደሚራመዱ፡ ሰቶኪንጎቻቸው ወደ ታች ጠቅልለው፡ ተጣብቃ ትራመዳለች፡ በምታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ፡ ትውረገረጋለች። በትክክል፡ ልክ አሁን እንደሚያደርጉት ነው። የወንድ ልብስ ይለብሳሉ፡ ይህም በእግዚአብሔር ዘንድ አሰጸያፊ ነው።

152 ቀደም ሲል፡ አንድ ኃይማኖታዊ ማሕበር፡ ወደ አንድ ነገር ሲገቡ አይቼ ነበር... በየምሽቱ ወደሚያካሂዱት አንዳንድ ዝግጅቶች ጋር ሲሄዱ፡ ሴቶቹ ሁሉ የለበሱት ነገር ቦላሌ-... ወ—ወይም ማን ነው—ማን ነበር የምትሉት? ቁምጣዎች ሳይሆኑ፡ ሌላኛው አይነት ነገር። አዎን፡ ታይት መሳዮች። ወይም እነዚያን የመሳሰሉ ነገሮች ናቸው። ሁሉም ለብሰው... እንደ ፔዳል ፑሽ ያስፈልጋቸዋል፡ እና፡ ወንድሜ፡ ሰፋቱ **ይሄን** ያክላል። ትክክል ነው። **ፔድ**

የሚለው ቃል **ፔደስትሪያን** ከሚል የወጣ ነው፡ ትርጉሙም “በእግር ስር” ማለት ነው፡ በትክክል የሚያስፈልጋቸው ያ ነው። በትክክል።

153 አቤት፡ እናንተ ግን፡ “መቼም፡ አሁን፡ እንደሚመስለኝ ቀሚስ ከምትለብስ ያንን ስትለብስ ጨዋ ያስመስላታል ብዬ እሰባለሁ፡” ትላላችሁ።

154 እግዚአብሔር እንዲህ ብሎታል፡ “ሴት እንደዚያ አይነት ልብስ ስትለብስ በፊቱ አስጸያፊ ነው... ” እና ሴት ፀጉሯን እንደ ወንድ ስትቆርጥ... እግዚአብሔር ሴትን ሴት እንድትመስል፡ እንደ ሴት እንድትለብስ፡ እንደ ሴት እንድትሆን ይፈልጋል።

155 ወንዱንም **እንዲህ** የተንጠለጠለ ወደ ጎን የወረደ ነገር እንዲኖረው አይፈልግም፡ እንዲሁም ደግሞ፡ እንደ ዳክዬ ራሱ ላይ ወደ ኋላ እንዲህ የተቀመጠ ነገር አይኑረው። ወንድ እንዲመስልለት ይፈልገዋል። አዎን፡ ወዳጄ። አቤት፡ ጾታቸውን መለየት እስኪያቅታቸው ድረስ በጣም ሴታ ሴት ልብስ ይለብሳሉ። አሁን በዚህ ዘመን የመጡብን ቢትኒኮች እና ሌላ ነገሮች ሁሉ፡ እንደው——በጣም ያሳዝናል። በመጨረሻ ዘመን ላይ መሆናችን እያስደነቅም፡ በዚህች ዓለም ላይ እግዚአብሔር ቁጣውን ሊያፈስባትና ሊያቃጥላት ከሆነ በቀር ምንም የቀረ ነገር የላትም። ይኼው ነው። ጻዲቁ እና ቅዱሱ አምላክ ከዚህ ሌላ ምንም ማድረግ አይችልም።

156 የኢየሱስ ክርስቶስን ደም አሳድፈዋል! የራሳቸውን ቀኖና አድርጓል! ድርጅት ውስጥ ገብተዋል! እንዲሁም... ወደ ኋላ የዞረ አንገትጌ ያጠለቀ አንድ ምሁር... ወይም አንድ ቅዱስ አቡን፡ ይመጣና “የተባረካችሁ ልጆቼ፡” ይላቸዋል። ይህ ግን ከሴት አሳማ ንግግር የዘለለ አይደለም።

157 ዛሬ ማታ የሚያስፈልገን፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እና ወደ መንፈስ ቅዱስ፡ እና ከሞት ወደ ተነሳው የክርስቶስ ኃይል፡ ወደ ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ገብቶ ምልክቶችን እና ድንቅ ተአምራትን ወደሚያደርግበት መመልስ ነው እልሃለሁ ወንድሜ። አሜን! ወንጌል ያ ነው። አዎን።

158 ስለዚህ... አዎን... እውነት ነው፡ እንዲሁ፡ አፍርቷል። ሪ——ሪ——ሪቫይቫሉ፡ በዚያ በሪቫይቫሉ ምክንያት ያደረጋቸው መልከ ምልካም ነገሮች አሉ። ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስን አላፈራም። እስከዚህ እስከ ሎዶቅያ ዘመን፡ እስከ ጴንጤቆስጤ ዘመን ድረስ ያንን ፍሬ አላመጡም። የሆነ ነገር ግን አድርጓል። ይህ ሪቫይቫል ያደረገው ነገር አለ እንዲህ እስኪባል ድረስ፦ “እስኪሞት ድረስ ዝም አትበለው፡ እየጨመርክ ማጠናከርህን ቀጥል።” አያችሁ?

159 ለሕዝቡ እንደገና ነፃ መጽሐፍ ቅዱስ አፍርቷል። የሉተራን ዘመን ነፃ መጽሐፍ ቅዱስን አፍርቷል። ማተሚያቸውን አዘጋጅተው ለዓለም መጽሐፍ ቅዱስ መስጠት ጀመሩ። ለዚህ ስራቸው እግዚአብሔር ሉተራኖችን ይባርክ! አዎን፡ ወዳጄ። መጽሐፍ ቅዱስን እንደገና በምእመናን እጅ ውስጥ አስገቡት፡ በቀሳውስት እጅ ብቻ ነበርና። ለማየት እንኳ በጭራሽ አይቻልም ነበር፡ ምክንያቱ ጳጳሱ ከተናገረ፡ እርሱ አምላክ ስለነበረ፡ እርሱ የሚለው ነገር ሁሉ፡ ይጸናል።

160 ስለዚህ አሁን፡ የሉተራን ሪቫይቫል፡ ፍላጎታቸው፡ “ማጠናከር” ሆነ። አሁን መጽሐፍ ቅዱስን በእጅህ ይዘሃል፡ ስለዚህ አሁን አንብበው! እመነው! በመደርደሪያው ላይ አስቀምጥተህ፡ “እንግዲህ፡ መጽሐፍ ቅዱስ አለን፡” አትበል። ያንን ምንም አይጠቅማችሁም። ዛሬ በጴንጤቆስጤ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን

ቁጭ አድርገው፡ ሌላ ሰው የሚናገረውን የሚጠብቁ በጣም ብዙ ሉተራኖች አሉ። ወንድሜ፡ ቃሉን አንብበው! “ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸውና፡ መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፡” አለ ኢየሱስ። “በእነሱ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታስባላችሁ።” ማድረግ ያለባችሁ ነገር፡ ቃሉን ማንበብ ነው!

161 ስለዚህ፡ እንዲህ ብቻ አለው፡ “ያንን ጠብቅ፡ እ... እንዲጠፋ—አትፍቀድ።” እንዲጠብቁት የፈለጋቸው ሌላ ነገር፡ በእነርሱ ዘንድ የቀረች ትንሽ ጥንካሬ ነበረች፡ ያም... የሉተራን ሪቫይቫል፡ ሁለተኛው ያደረገው ነገር፡ የጽድቅን ትምህርት ወደ ብርሃን ማምጣቱ ነው። ካቶሊኮች ስለ ጽድቅ አያነሱም፡ ራሷ ካቶሊክ ቤተ ክርቲያን ናት።

162 ልክ እንደዚያ ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ ከአየር ሰዓት እንዳወረዱት አይነት ቄስ ነው። “በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ሌላ መዳን የለም፡” ብሎ ተናገረ። መዳን በክርስቶስ ነው እንጂ፡ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አይደለም፡ በፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን አይደለም። መዳን፡ በክርስቶስ ነው። የካቶሊኮች እምነት ግን... ቤተ ክርስቲያን የምትለውን ነው እንጂ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ቢል ግድ የላቸውም። አያችሁ? ምንም ልትሏቸው አትችሉም፡ ምክንያቱ እነርሱን የምትናገሩበት ምንም አይነት—ምንም አይነት መንገድ የለም። ግድ የላቸውም። የያዙት ነገር አላቸው... ስለ ካተኪዝም፡ ወይም እንደነዚያ የመሳሰሉ ነገሮች ላይ መነጋገር ትችላላችሁ፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ከመጣችሁ ግን፡ በቃ “ዋናው የቤተ ክርስቲያኒቱ ቃል ነው፡” በማለት እንዲሁ ያ—ያጣጥሉታል።

163 ኢየሱስ ግን፡ በዚህ ነገር ላይ፡ ኢየሱስ ራሱ ሲናገር እንዲህ አለ፦ “ማንም አንዳች ቢያጎድልበት ወይም ምንም ቢጨምርበት፡ ድርሻውን ከህይወት መጽሐፍ ይጎድልበታል።” ኢየሱስ እንዲህ አለ፦ “የሰው ሁሉ ቃል ውሸት ይሁን፡ የኔም እውነት ይሁን። ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አያልፍም።” ልክ ነው? ውንድሜ ሆይ፡ ነገሩ፡ ይኸው ነው።

164 የእግዚአብሔር ቃል አማኝ ነኝ! በትክክል። ደግሞም እግዚአብሔር **በዚያ** የሚናገረውን ቃል ብቻ ሳይሆን፡ ያንን ቃል **እንዲያረጋገጥልኝ** ክርስቶስን በእኔ እንዲኖር፡ መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጠኝ የሰማይ አባትን እለምነዋለሁ። የዘላለም ሕይወት እንዳገኘሁ አውቃለሁ፡ ጸጋው ስለ ሰጠኝ እንጂ፡ ስለሚገባኝ አይደለም። ዓለቱ ያ ነው። “በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡” ብሏል።

165 እሺ እንግዲህ፡ ስለ ጽድቅ። በጣም ጥሩ። እንግዲህ ነገሩ እንዲህ ነው፡ እንዳይሞት ሊጠነቀቁለት የተገባቸው ነገር ካመጡት በኋላ፡ ይህ ማለት፡ እንደገና መጽሐፍ ቅዱስን በእጃቸው መያዛቸው ነው። ያንን ያደረጉት ሉተራኖች ናቸው። ሌላ የነበራቸው ነገር ደግሞ “ጽድቅ በእምነት፡” የሚል አስተምህሮ ነው። ሉተር ያስተማረው ይህ ነው፡ ይህ ዶክትሪን የሱ እንደሆነ ሰው ሁሉ ያውቃል። ጽድቅ-... ያ ምን ያህል ፍጹም እንደሆነ አይታያችሁምን? ከዚያ በመቀጠል ቅድስና በማለት ዌስሊ ተከተለ፡ አሁን ደግሞ ጴንጤቆስጤዎች የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ይዘው ብቅ አሉ። በቃ በሚደንቅ መልኩ። አሁን እኔ...

166 “ጥቂት ነገሮች አሉህ፡ አሁን በደንብ አጥብቀህ ያዛቸው፡ እንዲሞቱም አ—አትፍቀድላቸው። እንደሌባ ፈጥኜ እመጣብሃለሁ፡ በደንብ አጥብቀህ ካልያዝካቸው እንደገና ወደ ኃይማኖት ተቋም ትመለሳለህ።” ያደረጉትም ያንኑ ነበር፡ እንደተባለው፡ ወደኋላቸው ተመለሱ። “እንደገና ወደ ኒቆላውያኖች ትመለሳለህ፡ ምክንያቱም ወደ ኋላህ ወደ ኃይማኖት ተቋም ትሄዳለህና። እንግዲህ ጽና! መጽሐፍ ቅዱስ አንብብ፡ በጽድቅም ቀጥል፡ ወደፊት ቀጥል።” ከዚያ የሚወጡ ጥቂት ቅሪቶች ግን አሉ። ትንሽ ቅሪት።

167 በኋላ፡ ሉተር፡ በመጀመሪያ መጣ፡ ከዚያ ዝዊንግሊ ተከተለው፡ ከዚያ በመቀጠል፡ ካልቪን፡ ከዚያም፡ ዌስሊ እስኪመጣ ድረስ፡ ሌሎችም ነበሩ። ነገር ግን መቀደሰን የሚያስተምሩ ጥቂት ቅሬታዎች ከዚያ ወጡ። ከቅድስናም ጥቂት ቅሬታዎች ወደ መንፈስ ቅዱስ ደረሱ። አያችሁ፡ ትንሿ ቅሪት፡ ከዚያ ጀምራ ይሄን ያህል ርቀት፡ ያ—ነገር ህያው እንዲሆን አስጠብቃ ቆየች። በጣም ጥሩ።

168 በሶስተኛ ደረጃ፡ ግን፡ ከእርሱ ጋር ብዙ የአረማውያንን የትምህርት ዓይነቶች አመጡ፡ ለምሳሌ፡ የኃይማኖት ተቋም፡ ሐሰተኛ ጥምቀት። እና፡ እንዲሁ አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ በማለት፡ እየረጩ እና ልዩ ልዩ ነገሮች እያደረጉ መጡ። ካቴኪዝምን አስተዋወቁ። በእውነት… በእውነቱ ከተባለው ስም ጋር… ይጣጣማሉ… እዚህ ላይ ኢየሱስ የተናገረው፡ “ህያው እንደመሆንህ ስም አለህ፡ ሞተህማል።” ይህ ትክክለኛ ነው። በጣም ጥሩ።

169 በአራተኛ ደረጃ፡ ተሐድሶው ብዙዎቹን ያጌጡ ንዋየ ቅድሳት—እና የአምልኮ ሥርዓቶች እና ልዩ ልዩ ነገሮችን ጠራርጎ መውሰዱ የማይካድ እውነት ነው፡ ነገር ግን ተሃድሶን ለማምጣት እና ለማቃናት በቤተ ክርስቲን ላይ አልተሳካለትም፡ በሚከተሉት ምልክቶች የወንጌልን ሙሉ ትምህርት መመለስ አልቻለም። የሉተራን ቤተ ክርስቲያን ይህ በጭራሽ አልነበራትም። በጭራሽ አልነበራቸውም፡ በዌስሊ ዝመንም እንዲሁ በጭራሽ አልነበራቸውም። ይህ የተገኘው በዚህ በሎዶቅያ ዘመን መጨረሻ ላይ ነው።

170 አሁን፡ ወደዚያ ስንገባ፡ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት እንመለሳለን እና በትክክል እንዴት እንደናፈቁት አሳያችኋለሁ። ያ ነገር አልነበራቸውም… የመንፈስ ቅዱስ ሪቫይቫል አላቃኙም።

171 ከጣኦታት ተመልሰዋል፡ ከጣኦታት መመለሳቸው፡ እውነት ነው። ጣዖቶቹን ከቤተክርስቲያን አሰወግደዋል፡ ማርያም፡ እና ዮሴፍን፡ እና—ጴጥሮስን፡ ጳውሎስምን፡ ሁሉንም አውርደዋል። ከጣዖታት ቢመለሱም፡ ወደተነሣው ክርስቶስ ግን አልተመለሱም። ሉተር ከጣዖታት መልሷቸዋል፡ ይሁን እንጂ ወደ ፖለቲካ ወይም እና—ወደ ኃይማኖት ተቋም ያመዝን ነበር፡ እራሳቸውን ሌላ ድርጅት ለመመስረት (እንደ መጀመሪያው አይነት ምስል) ለማድረግ እና በኃይማኖት ተቋም በልጠው ለመታየት ብቻ ነበር።

172 እስከ አሁን ድረስ ውጊያ ላይ ናቸው። ሜቶዲስቶች ሌሎቹን… ባፕቲስቶቹን በሙሉ ሜቶዲስት እንዲሆኑ ይፈልጓቸዋል። ሉተራን ሁሉ ደግሞ ባፕቲስቶች እና ሜቶዲስቶች ሉተራኖች እንዲሆኑላቸው ይፈልጋሉ። ጴንጤቆስጤዎችም ባፕቲስቶች፡ ሉተራን፡ እና ሌሎች በሙሉ፡ ጴንጤቆስጤ እንዲሆኑ ይፈልጋሉ። አያችሁ፡ ወደ ተቋማቸው መጨመር ብቻ ነው። ይህ ግን

ከመጀመሪያ የእግዚአብሔር ፕሮግራም አይደለም። የእግዚአብሔር የተሃድሶ ፕሮግራም ከመጀመሪያው የነበረውን መልሶ የማምጣት ነው።

173 ተመልከቱ! የዚያ ትንሳኤ ለማድረግ! ለምሳሌ ይህ መፅሃፍ መሬት ላይ ቢወድቅ፡ በምትኩ ሌላ መጽሐፍ ማምጣት ማቃናት አይደለም፡ ትንሳኤ አይደለም። **ያንኑ** ዋናው ራሱ መምጣት አለበት። አሜን። ስለዚህ ቤተክርስቲያን በጨለማው ዘመን ከሞተች እና እንደገና **እዚህ** ጋር ሙሉ በሙሉ ጣኦት አምላኪ ከሆነች፡ ከዚያም ማቃናት፡ ያ... ያ ማደስ ነው፡ ተሐድሶ ነው፡ ይሁን እንጂ **መታደስ፡** እና **ዳግም መወለድ፡** ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እያችሁ? መታደስን፡ ተሐድሶን መለሱ እንጂ፡ ከብዙ ጣዖቶቻቸው እና ልዩ ልዩ ነገሮቻቸው ራቁ እንጂ፡ መንፈስ ቅዱስን ወደ ቤተ ክርስቲያን በፍጹም መመለስ አልቻሉም። ኦህ፡ የጌታ ስም የተባረከ ይሁን! ወንድም፡ እህቶች ሆይ፡ ይታያችኋል ወይ? መንፈስ ቅዱስን ፈጽሞ ወደ ኋላ መመለስ አልቻሉም፡ ምክንያቱ እውነተኛው የወንጌል ብርሃን የሚያመጣው... ኮፍያችሁን አጥልቁ አሁን። እውነተኛውን የወንጌል ብርሃን የሚያመጣው **የዚህችኛዋ** ቤተ ክርስቲያን መልአክ ነው። እንግዲህ፡ ያንን እሁድ እናየዋለን።

174 እንግዲህ፡ እነዚህ በብርሃን ላይ ብርሃን፡ እና ክርስትያናዊ ብርሃን ይኖራቸዋል፡ ሁሉም ወደዚያች ተቋም መሄዳቸው ግን አይቀርም። እሷን የሚቃወማት አንድ ግን ይነሣል። አዎን፡ ወዳጄ። እናም የእኔ በዚህ መድረክ ላይ መቆም እርግጠኛ እንደሆነ ሁሉ እርሱም እንዲሁ ቅሪቶችን ሰቦ ያወጣል። በትክክል እውነት ነው። እሱም በቀጥታ ወደ መጀመሪያው ይመለሳል። ከብሉይ እና ከአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት አውጥቼ ያንን እንደሚያደርግ አረጋግጥላችኋለሁ፡ ይህ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን መልአክ፡ በትክክል፡ እና በቀጥታ ወደ ዋናው ተመልሶ እዚህ ያሉ ነገሮች እንደገና ትንሳኤ ይሰጣቸዋል። ትንሣኤም **እዚህ** ጋር እንዳለው በዚህ ዘመን ይመጣል። እውነታው ይህ ነው።

175 ሉተር ግን ያመለጡትን፡ ቤተ ክርስቲያንን ሰቦ አወጣ። **ያመለጡትን**፡ ያም ቅድስ-... ቅድስና፡ አንድ ደረጃ ነው። ያመለጡትን፡ አንዱን እግራቸው ከአረማዊነት አወጣ። በጣም ጥሩ ነው። በሚቀጥለው፡ ሁለት እግር ይወጣል። ይኼው ነው።

176 ይህም ልክ እንደ... በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከቤተ መቅደሱ ጀርባ የሚፈስ ውሃ—እንደነበረ አስተውላችኋል? ውኃው እስከ ጉልበቱ ድረስ ሲደርስ አየሁ አለ፡ ከዚያም በመቀጠል፡ ውሃው እስከ ወገቡ ድረስ ደረሰ፡ ቀጥሎም፡ ከጭንቅላቱ በላይ አለፈ። ነገር ግን ከጭንቅላቱ በላይ ሲወጣ፡ መዋኘት ወዳለበት ሁኔታ ደረሰ። እያችሁ፡ መዋኘት ነበረበት።

177 እኛም አሁን ወይ መዋኘት ወይም ወደ መሰጠም ወዳለብን ሁኔታ እየደረሰን ነው። ይኸው ነው። ወይ አስጥሞ ሙሉ በሙሉ ውጦ ያሰወግዳችኋል፡ ወይም፡ አንድ ያደርጋችኋል። ስለዚህ፡ መዋኘት ወይ መሰጠም ነው! ሃሌ ሉያ! ኦህ፡ በመንፈስ ቅዱስ በጣም ደስ ብሎኛል! እናንተስ?

> እንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።
>
> እኔም አንዱ ነኝ... (ምንድን **ናቸው**? **ይህ**፡ **ያ**፡ ወይም **ያ**፡
> ወይም **ያ** አይደለም።)
> ... እንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፡ (ሃሌሉያ!)

አንዱ ነኝ፥ አንዱ ነኝ፥
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

ደስ አይልም ወይ? ስሙት፥

በላይኛው ክፍል ውስጥ ተሰብስበው፥
ሁሉም በስሙ ሲጸልዩ፥
በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ፥
የአገልግሎት ኃይል መጣና፥
ያን ቀን ለእነርሱ ያደረጋት
ለአንተም እንዲሁ ያደርጋል፥
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

ኦህ፥ አንዱ ነኝ፥ አንዱ ነኝ፥
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፥ (ሃሌ ሉያ!)
አንዱ ነኝ፥ አንዱ ነኝ፥
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

178 የተማሩ ነበሩን? አልነበሩም። አንዳንዶቹ ስማቸው እንኳን መጻፍ አይችሉም። እውነት ነው። ጴጥሮስ አይችልም ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እርሱ እንደሚለው፥ እርሱና ዮሐንስ አላዋቂና ያልተማሩ ሰዎች ነበሩ ይላል። ነገር ግን ከኢየሱስ ጋር እንደነበሩ ስለሚያውቁ፥ እነርሱን መስማት ግድ ነበር።

እነዚህ ሰዎች ምንም ባይማሩም፥ (ትምህርት።)
ዓለማዊ ዝና ባይኖራቸው፥ ("ኦህ፥ እግዚአብሄር ይባረክ፥
**እከሌ-እና-እከሌን** አየኋቸው።")
ሁሉም በዓለ ሃምሳን ተቀብለዋል፥
በኢየሱስ ስም ተጠምቀዋል፥
አሁን፥ በቅርቡም በሩቁም ለሁሉ ይነግራሉ፥
ኃይሉ አሁንም አንድ ነው ይላሉ፥
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

ኦህ፥ አንዱ ነኝ፥ አንዱ ነኝ፥
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፥
አንዱ ነኝ፥ አንዱ ነኝ፥
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

179 ናንተስ በዚህ ደስ አይላችሁምን? አንዱ በመሆኔ እጅግ ደስተኛ ነኝ። ከማውቃቸው ከማንኛውም ሌሎች ነገሮች ይልቅ ከእነርሱ አንዱ ብሆን እመርጣለሁ። ኦህ፥ የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንት ከመሆን ወይም በዓለም ላይ ንጉሥ ከመሆን ከእነርሱ አንዱ ብሆን እመርጣለሁ። ይሻለኛል… ለምሳሌ ኢየሱስ ቢመጣና፥ እንዲህ ቢለኝ፥ "ዕድሜህ ወደ ሀያ አመት መልሼ የበላይ አለቃ አደርግሃለሁ፥ የሃያ አመት ሰው ሆነህ፥ በዚህ ምድር ዕድሜህ—አስር ሺ ዓመታት አደርገዋለሁ፥ የዓለም ሁሉ ንጉስ አደርግሃለሁ፥ አንድም ቀን አትታመምም፥ ራስ ምታት አይዝህም፥ ነገርህ ሁሉ ደስታና ፈንጠዚያ ይሆናል፥ የምድርም ሁሉ ንጉሥ ሆነህ፥ አሥር ሺህ ዓመት መኖር ይሻልሃል፥ ወይስ አሁን እንደሚገጥምህ ውጣ ውረድ ጋር ከእነርሱ ጋር አንዱ መሆን ትመርጣለህ ቢለኝ?"

180 “አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፡” ባልኩት ነበር! ከአሥር ሺሕ ዓመታት በኋላስ፡ ምን ይፈጠራል? ይህ ግን ዘላለማዊ ነው። ወንድሜ ሆይ፡ የመጣው እንዴት ነው? ኦህ፡ የመጣው በደሙ ነው። ትክክል ነው። የመጣው በብዙ ውጣ ውረድ ነው፡ እግዚአብሔር ሥጋ ሆኖ በእኛ በማደሩ የመጣ ነው፡

ከረጅም ጊዜ በፊት፡ የተፈጠረውን አውቃለሁ በበረት ውስጥ፡
ሰዎችን ከኃጢአታቸው ለማዳን ሕፃን ተወለደ።
ዮሐንስ በባሕሩ ዳርቻ፡ አየው በጉን ለዘላለም፡
እነሆ፡ በቀራንዮ የተሰቀለው፡ ክርስቶስ።

ኧረ፡ ያን የገሊላ ሰው፡ የወደድኩት የገሊላ ሰው፡
ለእኔ በጣም ብዙ አድርጎልኛልና።
ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር ብሎኛል፡ መንፈስ ቅዱስን በውስጤ አሳድሮልኛል፡
ኧረ፡ ወደዋለሁ፡ ያን የገሊላ ሰው እወደዋለሁ።

በጉድጓዱ አጠገብ ያገኛት ሴት፡ ኃጢአቶቿን ሁሉ ነገራት፡ (እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ነው።)
በዚያን ጊዜ እንዴት አምስት ባሎች እንደነበሯት።
የኃጢአት ይቅርታን ሁሉ አገኘች፡ ጥልቅ ሰላም በልቧ ተቀመጠላት፡
ጮኸች “ኑ ይህን የገሊላ ሰው እዩት!” እያለች፡

ኧረ፡ ያን የገሊላ ሰው ወደዋለሁ፡ የገሊላ ሰው፡
ለእኔ በጣም ብዙ አድርጎልኛልና።
ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር ብሎኛል፡ መንፈስ ቅዱስን በውስጤ አሳድሮልኛል፡
ኧረ፡ ወደዋለሁ፡ ያን የገሊላ ሰው ወደዋለሁ።

አንድ ቀን ቀራጩ ወደ መቅደስ ሊጸልይ ሄደ፡
“አቤቱ፡ ጌታ ሆይ ማረኝ!” እያለ ጮኸ፡
ስለ ኃጢአቱ ሁሉ ይቅርታን አገኘ፡ ጥልቅ ሰላም በውስጡ አደረ፡
“ኑ ይህን የገሊላ ሰው እዩት፡” እያለ ጮኸ።

እኔ ተመቸኝ። እናንተንስ?

አንካሳው ተራመደ፡ ዲዳው ተናገረ፡
ያ ኃይል በባህር ላይ በፍቅር ተናገረ፡
አይነ ሰውሩም ማየት ቻለ፡ ከማን ሊሆን እንደሚችል አውቃለሁ
የዚያ የገሊላ ሰው ምሕረት ነው።

ከእኔ ጋር ዘምሩት፦

ኧረ፡ ያን የገሊላ ሰው ወደዋለሁ፡ የገሊላ ሰው፡
ለእኔ በጣም ብዙ አድርጎልኛልና።

ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር ብሎኛል፡ መንፈስ ቅዱስን
በውስጤ አሳድሮልኛል፡
ኧረ፡ ወደዋለሁ፡ ያን የገሊላ ሰው ወደዋለሁ።

181 እናንተስ አትወዱትም ወይ? ኦህ፡ ማይ! ይህ መልካም፡ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል፡ አቤት፡ እንዴት እንደምወደው። በሙሉ ልቤ እወደዋለሁ። ዛሬ ማታም ከእነሱ ጋር ስለተቆጠርኩ በጣም ደስ ብሎኛል፡ እንደ ወንድሞች እና እህቶች አብረን ነን። ባፕቲስቶች፡ ሜቶዲስቶች፡ ፕሬስ-... ካቶሊክ፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ሌሎችም፡ እግዚአብሔር ከእያንዳንዱ የሕይወት ጎዳና አውጥቶን ወደዚህ ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ህብረት አምጥቶናል። የየትኛውም የኃይማኖት ተቋም አባል አይደለንም፡ እነርሱ ስለሚሰሩት ነገር የራሳቸው ጉዳይ ነው፡ እኛ ሚስጥራዊት መንግሥት ውስጥ ነን። በመንፈስ ቅዱስ፡ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስጢራዊ አካል ተጠምቀናል። ማን ናቸው? ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ የተጠማ ሁሉ፡ ይምጣ።

182 ኢየሱስም፡ “አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፡ አንዳቸውም አይጠፉም፡ በመጨረሻው ቀንም እንደገና አስነሳቸዋለሁ።” ኦህ፡ ማይ! በዚህ መሰውያ ላይ የምንዘምረው የድሮ መዝሙር ነበር፡ አሁን መዘመር እንችል እንደሆነ እንጃ፡ “ቤት፡ ቤት፡ አዎን፡ ቤት አለኝ፡ ከምንጩ በታች የተዘጋጀልኝ ቤት አለኝ።” እንደዚህ ያሉ የድሮ መዝሙሮች ትወዳላችሁ? አገባቡን የሚያውቅ ሰው ካለ፡ ቁልፉን ይጫወትልን። የት አለች የፒያኖ ተጫዋቻችን? እዚህ ናት? ወይንም ወንድም ቴዲ ወይም እዚህ ካሉት አንዳቸው? ከእነሱ? ኦህ፡ ማይ፡ የ—የትም አይታየኝም።

ቤት፡ ቤት፡ አዎን፡ ቤት አለ፡
በምንጩ ላይ ቤት አለልህ፡
ቤት፡ ቤት፡ አዎን፡ ቤት አለ፡
በምንጩ ላይ ቤት አለልህ።

183 ድሮ ዝማሬዎችን ትወዳላችሁ? እኔም ይሔኛውን እወደዋለሁ፡

በመስቀል ሞተ መድኃኒቴ፡
እኔን ለማዳን ከኃጢያቴ፡
ኦህ፡ በደሙ መረጨት ከጥፋቴ፡
ክብር ለስሙ!

ክብር ለስሙ! (ክቡር ሰሙ!)
ኦህ፡ ክብር ለ...

አይናችንን ጨፍነን እንዘምረው።

ኦህ፡ በደሙ መረጨት ከጥፋቴ፡
ክብር ለስሙ!

በድንቅ ከኃጢያት አዳነኝ፡
ኢየሱስ በእረፍት ውስጤ ኖረልኝ፡
በመስቀሉ እኔን አስገባኝ፡
ክብር ለስሙ!

ክብር ለስሙ! (ያን ክቡር ሰም!)

ክብር ለስሙ! (ክቡር ስም!)
በደሙ መረጨት ከጥፋቴ፡
ክብር ለስሙ!

184 አሁን ይህን ቀጣይ አዝማች በምንዘምርበት ጊዜ ከፊት፡ ከኋላ፡ ከጎናችሁ፡ ካለው ሰው ከአንድ ሰው ጋር እጅ ለእጅ ተጨባበጡ።

ወደ ሃብታም ጸጋው ኑ ቅረቡ፡
ምስኪን ነፍሳችሁ ከእግሩ ስር አኑሩ፡
ኦህ፡ ራዜ ወሰዳችሁ፡ ፍጹማን ሁኑ፡
ክብር ለስሙ!

ክብር ለስሙ! (ያን ክቡር ስም!)
ክብር ለክቡር ስሙ!
በደሙ መረጨት ከጥፋቴ፡
ክብር ለስሙ!

ኦህ፡ በጣም ወደድኩት። እናንተስ?

ክብር ለስሙ! (ክቡር ስሙ!)
ክብር ለስሙ!
በደሙ መረጨት ከጥፋቴ፡
ክብር ለስሙ!

185 ኦህ፡ ማይ! እኔ በጣም ደስ ብሎኛል። እናንተስ? ደስ ብሎኛል ባለጸጋ እና ምቹ ወደሆነው ምንጭ በመምጣቴ፡ ምስኪን ነፍሴን በአዳኝ እግር ስር በመጣሌ።

186 አንድ ቀን፡ አንድ የአስራ ሰምንት አመት ወጣት ሆኜ፡ ከጌታ ዘንድ ሰሸሸ፡ ትዝ ይለኛል። ወደ ምዕራብ አቀናሁ፡ አባቴ ጋላቢ ስለነበረ... እኔም ሄጄ፡ ፈረሶችን መግራት ፈለግሁ። ብቻ ምን ልበላችሁ በልቤ ውስጥ የሆነ ርሃብ ነበረ። አቤት፡ እላችኋለሁ!

187 ወደ ባፕቲስቱ ሰባኪ ወረድኩ፡ እሱም እንዲህ አለ፡ “ተነሥተህ ‘ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡’ ብቻ በል፡ እኛ ሰምህን በመጽሐፉ ላይ እንመዘግብልሃለን።” ያ አላረካኝም።

188 በሄድኩበት ሁሉ አንድ ሰው... የሰባተኛው-ቀን አድቬንቲስት፡ ጥሩ ሰው፡ ለመጠየቅ ሄድኩኝ፡ ወንድም ባርከር ይባላል፡ መልካም ወንድም፡ “ቢሊ፡ ናና የጌታን ሰንበት ተቀበል፡” አለኝ። (አሁን አግኝቼዋለሁ።) እሱ ግን “የሰንበት ቀን፡” አለኝ። እኔም “አይ፡ ይህ እንኳ ሊሆን አይችልም፡” ብዬ አሰብኩ። አያችሁ።

189 ወደ ምዕራብ ሄድኩ፡ እና አሰብኩ... በዚያ ቀን ማታ ላይ፡ ከብት እገታ ላይ ውለን ተመልሰን መጣን። እና፡ ታውቃላችሁ፡ ኮርቻውን እና የማረፊያችሁ ሻንጣ አውርዳችሁ፡ እንዲህ ታነጥፉታላችሁ፡ ኮርቻውን እንደ ትራስ ትጠቀማላችሁ። እና በዚያ ሌሊት፡ በእነዚያ ባረጁ የጥድ ዛፎች ስር ተኛቼ ነበር። ያን ጊዜ የቀን ተረኛ ነበርኩ፡ እና የሌሊት ተረኞች ከብቶቹን እያወረዱ ነበር። በዚያም “ሰሊም፡” የሚሉት፡ ከቴክሳስ የመጣ ሽማግሌ ነበር፡ ጊታር ነበረው—እና ይጫወት ነበር፡

ክብር ለስሙ!

190 አንደኛው ሰው ደግሞ ማበጠሪያውን ቁራጭ ወረቀት አጣብቆበት፡ በትንፋሹ ይጫወተው ነበር። [ወንድም ብራንሃም **ክብር ለስሙ** አንጎራጎረ—አርታዒ።] ሌሎች ዝማሬዎችም ይዘምሩ ነበር፡ ካውቦይ ባላድን፡ እና ያንን **በመስቀሉ ስር**።

191 አቤት! ዞር አልኩና፡ ብርድ ልብሴን ከንጭንቅላቴ በላይ **እንዲህ** ጣል አደረግኩት። እንደገናም፡ አይኔን አነሳሁና አየሁ፡ ከዋክብትም በዚያ ተንጠልጥለው በዛፎችና በተራሮች መካከል የተንጠለጠሉ ይመስሉ ነበር። ከጥድ ዛፎች መካከል የሚንሾካሾከው ዕድሜ ጠገቡ ድምጽ፡ "አዳም ሆይ፡ ወዴት አለህ? " የሚለው ነበር፡

192 ከሶስት ሳምንታት በኋላ ወደ ከተማው ወረድኩ፡ እና ወጣቶቹ ሁሉ ሰክረዋል፡ እኔ ግን አልጠጣሁም። አንድ በአንድ፡ ሁሉንም በመኪና እየጫንኩ መውሰድ፡ ግድ ሆኖብኛ ነበር። ወጥተው አውራጣቶቻቸው ስር እየተተኳኮሱ፡ እና ሌላም ነገሮች እያደረጉ፡ አደገኛ ነገር ያደርጉ ነበር፡ ቀጥ ያለ መስመር ያሰምራሉ፡ ከዚያም ወደዚያ መውጣት ማን ይችላል በአምስት ዶላር ይጫወታሉ፡ ታውቃላችሁ፡ የእግረኛ መንገዱን እንደዚያ መውጣት የቻለ አልነበረም። እና ገንዘባቸው ከተቀበሉ በኋላ፡ ሰካሩ እስኪለቃቸው ድረስ ሁሌም እንዲሁ ናቸው።

193 እና ሁሉም ሰክረዋል እኔም በዚያ ሆኜ፡ ራቅ ብዬ ተቀምጫለሁ። "አቤት! አቤት!" አልኩና አሰብኩት፡ ከሠላሳ-አምስት ዓመታት በፊት፡ ወይም ሠላሳ-አምስት፡ ይመስለኛል፡ ከሠላሳ-አምስት ዓመታት በፊት ነው። እና በዚያ፡ ብቻዬን ቁጭ ብዬ ነበር። ያን ጊዜ ፎኒክስ ትንሽዬ መንደር ነበረች፡ እና ከዊክንበርግ ወደዚያ ወርደን ነው። እኔም ቁጭ ብዬ ሳለሁ፡ አንዲት እስፓኒሽ ሴት እየተውረገረገች ወደዚያ አቅጣጫ መጣች፡ ከራሴ ወደ ኋላ ላይ ትልቁን ኮፍያ እንዲህ አንጠልጥዬ ቁጭ ብያለሁ፡ ትንሽዬ መሃረብ ጣል አርጋ አልፋኝ ሄደች፡ እና፡ ደሰም ሰላላለኝ። "ሄይ፡ ማን ነሽ አንቺ መሃረብሽን ጥለሻል፡" አልኳት።

194 ከዚያ ከመንገድ ማዶ ላይ የሆነ ድምጽ ሰማሁ፡ እና ወደዚያ ወጣሁ። እና ከእነዚያ የፈረሰ ግልቢያዎች ወጥቶ የተቀየረ አንድ ሽማግሌ አየሁት፡ ፍፊቱ ላይ ብዙ ጠባሳዎች ይታያሉ፡ እንባ በጉንጮቹ ላይ እንዲህ እየፈሰሱ፡ በጊታር፡ መዝሙር ይዘምራል፡

ክብር ለስሙ!

195 ኦህ፡ ማይ! እንባዎቹ ፊቱ ላይ እየፈሰሱ፡ ቆም አለና እንዲህ ተናገረ፡ "ወንድሜ ሆይ፡ ይህን ድንቅ ክርስቶስን እስክትቀበል ድረስ ምን ማለት እንደሆነ አይገባህም።"

ክብር ለስሙ!

196 ያን ትልቅ ኮፍያ ወደ ታች አወረድኩትና ሄድኩኝ። ኦህ፡ ማይ! ከሱ መደበቅ አትችሉም። እናንተም አሁን ወጥታችሁ እሱን መከተል ትችላላችሁ። አቤቱ፡ እሱ ድንቅ ነው! አዎን፡ ነው።

በድንቅ ከኃጢያት አዳነኝ፡

ኢየሱስ በእረፍት ውስጤ ኖረልኝ፡ (በውስጤ **ኖረልኝ**!)
በመስቀሉ እኔን አስገባኝ፡
ክብር ለስሙ!

ክብር ለስሙ! (ስሙ!)
ክብር ለስሙ!
ኦህ፡ በደሙ መረጨት ከጥፋቴ፡
ክብር ለስሙ!

ኦህ፡ ወደ ሃብታም ጸጋው፡ ኑ ቅረቡ፡
ምስኪን ነፍሳችሁ ከእግሩ ስር እኑሩ፡
ኦህ፡ ዛሬ ወስዳችሁ፡ ፍጹማን ሁኑ፡
ክብር ለ...

እሁን እንገታችንን ዝቅ፡ እጃችንን ወደ ላይ፦

ክብር ለስሙ! (ክብር፡ ክብር!)

(እግዚአብሔር ሆይ!) (ክቡር ስም!)

በደሙ መረጨት ከጥፋቴ፡
ክብር ለስሙ!

197 ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! እንነሳ። ኦህ፡ ትንሽ ደቂቃ ብቻ፡ ትንሽ፡ ቆዩ።

[አንዲት እህት በልሳን ተናገረች፡ ሌላ ወንድም ተረጎመው—እርታዒ።] አዎን፡ ጌታ ሆይ።

198 እንግዲህ ምን እንደ ሆነ የማያውቁ አንዳንዶች ቢኖሩ፡ ጴንጤቆስጤ ማለት ያ ነው፡ መንፈስ ቅዱስ እየተናገረ ነው። ኢየሱስም አለ፡ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፡ ወንጌልንም ስበኩ። ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል። በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፡ በድውዮች ላይ እጃቸውን ይጭናሉ፡ እነርሱም ይድናሉ።" እሱ የተናገራቸው ሁሉ፡ ይፈጸማሉ።

199 ኦህ፡ በጣም ደስ ብሎኛል። ቃሉን የሚያጸናው፡ መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ አያችሁ? ብርሃን፡ ተቀበሉ፡ አት—አትጠራጠሩት። ዝም ብላችሁ ተቀበሉት እንደ ልጅ ይቀበላችኋል ያሳድጋችኋል። መንፈስ ቅዱስ ይህን ማድረጉ በጎ ስለሆነ አይደለምን? መንፈስ ቅዱስ በእኛ ላይ።

200 እንዴ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እስታውሳለሁ፡ በየት በኩል እንደሚመጣባቸው አላወቁም ነበር፡ ጠላት እየመጣ ነበርና፡ መንፈስ ቅዱስም እንደዚህ ባለ አንድ ሰው ላይ ወረደና፡ ወዴት እንደሚሄዱ በትክክል ነገራቸው። እነርሱም ወጡ፡ እግዚአብሔርም ሌላውን ስራዊት ግራ አጋብቶ ዘረረላቸው። እውነት ነው።

201 ኦህ፡ አሁንም'ኮ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን እየኖርን ነን፡ አይደለንም ወይ? አሜን። መንፈስ ቅዱስ እስካለ ድረስ፡ ሁሌም እንዲያ ነው።

202 ኦህ፡ አሁን እንደቆምን መዝሙር እንዘምራለን፡

የኢየሱስ ስም ከአንተ ጋር ይሁን...

መልእክቱን አስታውሱ።

የዋይታና የሐዘን ልጅ፡
ደስታ እና ምቾት ይሆንሃል፡

በሄድክበት አይለይህ።

ድንቅ ስም፡ (ድንቅ ስም!) ኦህ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ (ያን ድንቅ ስም!) (ኦህ ውብ ስም!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

የኢየሱስ ስም ከአንተ ጋር ይሁን፡
ወጥመድ ሲኖር ይታደግሃል፡
ከከበቡህ ፈተናዎች፡
በጸሎት ያን ቅዱስ ስም ተንፍስ። (እግዚአብሄር ይመስገን!)

ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ (ድንቅ ስም!) ኦህ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

አዝማቹን ስሙት፡

የኢየሱስ ስም ከአንተ ጋር ይሁን፡
ወጥመድ ሲኖር ይታደግሃል፡
ከከበቡህ ፈተናዎች፡
ቅዱሱን ስም በጸሎት ተንፍስ።

ኦ፡ እንደገና እንዘምረው፡

የኢየሱስ ስም ከአንተ ጋር ይሁን፡
ወጥመድ ሲኖር ይታደግሃል፡
ከሚከቡህ ፈተናዎች፡
ቅዱሱን ስም በጸሎት ተንፍስ።

እራሳችንን ዝቅ እናድርግ አሁን፡

ድንቅ ስም፡ (ድንቅ ስም!) ኦህ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ስም! (ውብ ስም!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

**የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ዘመን** AMH60-1209

(The Sardisean Church Age)

**የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ተከታታይ ትምህርት**

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ታሕሳስ 9፡ 1960፡ ዓርብ ማታ፡ በዩ.ኤሰ.ኤ.፡ ጀፈርሰንቪል ኢንዲያና፡ ከሚገኘው ከብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org